# የገፀ-ባህርያት አሳሳል በከርታታው ልቦለድ

በ

ሳሙኤል ደመቀ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት
ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም
አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

# የገፀ-ባህርያት አሳሳል በከርታታው ልቦለድ

በ

ሳሙኤል ደመቀ

በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ-ጽሐፍ ክፍለ ትምህርት

ለአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጽሑፍ

አማካሪ
ሰላማዊት መካ

የቋንቋዎች ጥናት ተቋም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ 2001 ዓ.ም
አዲስ አበባ

## ምስጋና

- ይህንን ጥናት ስሰራ በገንዘብ፣ በምክር እንዲሁም በሀሣብ ሌት ተቀን ሳይቦዝኑ ለለፉልኝ ቤተሠቦቼ ልባዊ ምስጋናዬን አቀርባለሁ፡፡
- ይህ ጥናታዊ ጽሁፍ ተጀምሮ እስከሚፈፀም ድረስ ሙያዊ አስተያየት እየሠጠች ላማከረችኝ ለመምህርት ሰላማዊት መካ ከፍ ያለ ምስጋናን አቀርባለሁ፡፡
- ይህንን ጥናታዊ ጽሑፍ ሳዘጋጅ የሚያስፈልጉኝን መረጃዎች አብረውኝ በማሠባሠብ ለተባበሩኝ ጓደኞቼ በመላ "ውለታችሁን ፈጣሪ ይመልከትልኝ፡፡" እላለሁ፡፡

## አጠቃሎ

ይህ ጥናት “የገፀ-ባህርያት አሳሳል በከርታታው ልቦለድ” በሚል ርዕስ፣ በ1999 ዓ.ም በደራሲ ባህሩ ዘርጋው የታተመውን <u>ከርታታው</u> ረጅም ልቦለድ ይመለከታል፡፡የጥናቱ መነሻ ደራሲው ለመጀመሪያ ጊዜ ባሳተሙት በዚህ ልቦለድ ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህርያትን እንዴት እንደሳሉ ለመተንተን እና በገፀ-ባህርያት አሳሳል ወቅት ያሳዩት ድክመትም ሆነ ጥንካሬን ለመገምገም ነው፡፡ ከዚያም በተጨማሪ ደራሲው አዲስ የገፀ-ባህርያት አሳሳል ስልት መጠቀማቸውን ለማሳየት ነው፡፡

በጥናቱ ውስጥ የደራሲው የገፀ-ባህርያት አሳሳል እንዴት እንደሆነ ከመታየቱ በፊት ከዚህ ጥናት አስቀድሞ በገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ የተሰሩ የተዛማጅ ፅሁፎች ቅኝት ተደርጓል፡፡ ከዚያም ስለገፀ-ባህርያት አሳሳል ስልት ትወራዊ ዳራ ተሰጥቷል፡፡

በድርሰቱ ውስጥ ገፀባ-ህርያቱን ለመሳል በአንደኛ መደብ የትረካ አንጻር (እኔ ባይ) ተራኪ በስፋት ይታያል፡፡በዚህ ልቦለድ ውስጥ ደራሲው ትኩረት የሰጡበትና ጠንከር ብሎ የታየው ጉዳይ የገፀ-ባህርያት ውስጣዊ ባህሪ ላይ ሲሆን በአካላዊ ገለፃው ረገድ ደከም ብሎ ይታያል፡፡ ከንዑስ ገፀባ-ህርያት ይልቅ በዋና ገፀባ-ህርያት ላይ የተጠቀሙት አካላዊ ገለፃ ይህ ነው የሚባል አይደልም፡፡

በልቦለዱ የታየው የገፀባ-ህርያት አሳሳል ስልት እንብዛም ሆኖ ተገኝቷል፡፡ አብዛኛዎቹ ገፀባ-ህርያት ውጫዊ መልካቸውና ውስጣዊ ባህሪያቸው ተመሳሳይ መሆኑ ገፀ-ባህርያቱን ወደ ግጭት እንዳይገቡ ስላደረጋቸው የገሀዱ አለም ነፀብራቅ ይሆኑ ይሆን? የሚል ጥያቄ ያስነሳል፡፡ አንዳንዶቹ ገፀባ-ህርያት ወጥነት የጐደላቸውና ኢተአማኒ ናቸው፡፡ በመጽሐፉ የታየው ሙት መንፈስን የወከለው ገፀ-ባህሪ ለአገራችን አንባቢያን አዲስ በመሆኑ ስለሙት መንፈስ በመጠኑም እንዲያውቅ በመደረጉ ይደነቃል፡፡

በመጨረሻም ይህ ጥናት በጥናቱ ማጠቃለያ ስር የዚህን ልቦለድ ድክመትና ጥንካሬ በማውጣት ለማሳየት ሞክሯል፡፡ ገፀ-ባህርያቱ በአብዛኛው ተመሳሳይ አካላዊ መልክና ሕኒናዊ ባህሪ መያዛቸው ልቦለዱን ከድርሰት አፃፃፍ አንፃር ደካማ ሲያደርገው፤ በመጽሐፉ የተሳሉት ብዙዎቹ ገፀ-ባህርያት ቆራጥነታቸውና የአላማ ጽናታቸው እስከ ታሪኩ መጨረሻ መዝለቁ ከዘላቂነት አንፃር መጽሐፉ ያሳየው ጥንካሬ ነው፡፡

# ማውጫ


ርዕስ ገጽ

ምዕራፍ አንድ

1. መግቢያ

1.1 የጥናቱ ዳራ ........................................................................ 1

1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት........................................................ 2

1.3 የጥናቱ ዓላማ...................................................................... 3

1.4 የጥናቱ ወሰን...................................................................... 3

1.5 የጥናቱ ዘዴና አደረጃጀት......................................................... 4

ምዕራፍ ሁለት

2. ክለሳ ድርሳን

2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት......................................................... 8

2.2 ንድፈ ሀሳባዊ ዳሰሳ................................................................. 9

2.2.1 የገፀ-ባህርያት ምንነት ................................................ 9

2.2.2. የገፀ-ባህርያት አሳሳል በረጅም ልቦለድ........................ 10

2.2.3 ገፀ-ባህርያት በረጅም ልቦለድ ውስጥ............................ 12

2.2.4 የገፀ-ባህርያት አይነቶች............................................... 13

2.2.4.1 ውስብስብ ገፀ-ባህርያት................................ 14

2.2.4.2 አስተኔ ገፀ-ባህርያት..................................... 14

2.2.5 የገፀ-ባህርያት መልኮች............................................... 15

2.2.5.1 ውጫዊ ገፅታ............................................. 15

2.2.5.2 ውስጣዊ ገፅታ............................................ 16

2.2.6 የገፀ-ባህርያት አቀራረብ ዘዴዎች.................................. 16

2.2.6.1 ርቱዕ አቀራረብ........................................... 17

2.2.6.2 ኢ-ርቱዕ አቀራረብ........................................ 17

2.2.7 የገፀ-ባህርያት ዘላቂነት................................................ 18

2.2.8 የገፀ-ባህርያት ተአማኒነት ........................................... 19

ምዕራፍ ሦስት

3. የገፀ-ባህርያት አሳሳል በከርታታው ልቦለድ...................................... 20

3.1 የከርታታው ልቦለድ ታሪክ በአጭሩ......................................... 20

3.2 የከርታታው ልቦለድ ገፀ-ባህርያት አሳሳል ትንተና.................. 22

3.2.1 አያልቅበት አለሙ..................................................... 22

3.2.1.1 የአያልቅበት አለሙ አካላዊ መልክ ......................... 22

3.2.1.2 የአያልቅበት አለሙ ውስጣዊ ባህሪ ....................... 24

3.2.2 የከርታታው አልዩ ሙት መንፈስ. .................................................. 29
3.2.2.1 የከርታታው አልዩ አካላዊ መልክ ........................... 31
3.2.2.2 የከርታታው አልዩ ህሊናዊ ባህሪ ............................. 32
3.2.3 የአለበል አካላዊ መልክ እና ሕልናዊ ባህሪ ....................................... 36
3.2.3.1 የአለበል አካላዊ መልክ .......................................... 36
3.2.3.2 የአለበል ሕሊናዊ ባህሪ ........................................... 37
3.2.4 የጨቡዴ አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ ........................................ 38
3.2.4.1 የጨቡዴ አካላዊ መልክ ........................................... 38
3.2.4.2 የጨቡዴ ሕሊናዊ ባህሪ ........................................... 39
3.2.4.3 ጨቡዴ ለድርሰቱ ያመጣው ፋይዳ.......................... 39
3.2.5 አብዬ ሃምዛ........................................................................... 40
3.2.5.1 የአብዬ ሃምዛ አካላዊ መልክ ..................................... 40
3.2.5.2 የአብዬ ሃምዛ ሕሊናዊ ባህሪ .................................... 41
3.2.6 የዘነበች አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ ............................................. 42
3.2.6.1 የዘነበች አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ ..................... 42
3.2.6.2 የዘነበች ሕሊናዊ ባህሪ ................................................ 42
3.2.7 በከርታታው ልቦለድ የገፀ-ባህርያት አሳሳል መመሳሰል
በአካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ ......................................................... 43
3.2.7.1 የከርታታው፤ የአያልቅበትና የአያልቅበት
አባት ህሊናዊ ባህሪ መመሳሰል.................................. 44
3.2.7.2 የጨቡዴ ፤ የአብዬ ሃምዛና የዘነበች አካላዊ
መልክና ህሊናዊ ባህሪ አሳሳል መመሳሰል.................. 44
3.2.8 የከርታታው ልቦለድ መጽሐፍ የገፀ-ባህሪያት ስም፤
አሰያየምና የግጭት ሁኔታ...................................................................... 47
- ማጠቃለያ............................................................................................ 48
- ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው........................................................................ 50
- ዋቢ ጽሑፎች ........................................................................................ 51

# ምዕራፍ አንድ

# መግቢያ

## 1.1 የጥናቱ ዳራ

ስነ-ጽሑፍ የአንድን ሕብረተሰብ ማንነት እና ህይወት የሚያሳይ፣ እንዲሁም የሚተረጉም የምናብ ሥራ ሲሆን፤ በተዘዋዋሪም የአንድ አገርን ኢኮኖሚያዊና ልማታዊ ዕድገት የሚይፋጥን ድምፅ የለሽ መሣሪያ ነው፡፡ ደራሲም በኑሮ መነፅሩ የተመለከታቸውንና የታዘባቸውን የሰው ልጆች ሀዘን- ደስታ፣ ዕድገት - ውድቀት፣ ፍቅር-ጥላቻ፣ ሽፍጥ-እውነት ወዘተ.... በስነ-ጽሑፍ ውስጥ ይገልፃል-ያሳያል፡፡ በዓለምም ሆነ በአገራችን ስነጽሑፍ መፃፍ ከተጀመረበት ጊዜ አንስቶ በርካታ ደራስያን በተለያዩ ርዕሰ ጉዳዮች ዙሪያ የተዋጣላቸው የስነጽሑፍ ሥራዎችን ከሕይወት ልምዳቸው በመነሳት ለአንባብያን ሲያቀርቡ ኖረዋል-እየኖሩም ነው፡፡

በአሁኑ በ21 ኛው ክፍለ ዘመን ሰልጥነዋል የምንላቸው ሀገራት ከስልጣኔአቸው በስተጀርባ ስነጽሑፍ ትልቁንና አይነተኛ የሆነውን ሚና ተጫውቷል፡፡ በአገራችን በኢትዮጵያም ዘመናዊ የስነጽሑፍ ሥራዎች ማቆጥቆጥ ከጀመሩበት ጊዜ ጀምሮ እስካሁን ድረስ በርካታ የስነጽሑፍ ትሩፋቶች/ልቦለድ፣ስነግጥም፣ወግ፣ መጣጥፍ ወዘተ.../ ለሕዝብ ቀርበው አንባቢ እጅ ውስጥ በመግባት የራሳቸውን አሻራ ጥለው አልፈዋል፡፡

በ1990ዎቹ ማብቂያ ላይ ከተፃፉት ስራዎች መካከል <u>ከርታታው</u> የተሰኘው ልቦለድ ድርሰት አንዱ ነው፡፡ ደራሲው ከአሁን ቀደም በትርጉም ሥራዎቻቸውና በመዝገበ ቃላት ዝግጅት የምናውቃቸው ሲሆኑ፤ አሁን ደግሞ ከዕድሜና ከሥራ ልምድ እንዲሁም ካነበቧቸው መጽሐፍትና ከገበዩዋቸው ዕውቀት ተንተርሰው ይህን ረጅም ልቦለድ ለንባብ አብቅተዋል፡፡ ደራሲው ባህሩ ዘርጋው ሲሆኑ፣ መጽሐፉ የታተመው በ1999 ዓ/ም ለመጀመሪያ ጊዜ ሆኖ፤ በውስጡም ሶስት መቶ አስራ ሁለት ያህል ገፆችና አርባ ምዕራፎች አሉት፡፡ የታተመበት ቦታ ግን በውል አይታወቅም -አልተገለፀም፡፡

በዚህ ድርሰት ውስጥ ወደ ሃያ ሶስት የሚጠጉ ገፀ-ባህርያት ያሉ ሲሆን ሁለት ዋና ገፀ-ባህርያትና ሌሎቹ ንዑስ ገፀ-ባህርያት ናቸው፡፡ የዚህ ጥናት አቅራቢም ጣራ የነካ የስነጽሑፍ ሂስ የመስጠት ችሎታ ባይኖረውም ከስነጽሑፍ ትምህርት እና ከንባብ የተገኘውን እውቀትና ልምድ መሠረት በማድረግ መጽሐፉ ከገፀ-ባህርያት አሳሳል አኳያ ምን እንደሚመስል በተወሰኑ ገፀ-ባህርያት ላይ ትንተና በማድረግ ጠንካራም ሆነ ደካማ ጉኑን ለማየት ሞክሯል፡፡

በአንድ ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ በዋነኛነት /በመሠረታዊነት/ ከሚገኙት አለባውያን መካከል ዋናዎቹ ገፀ-ባህርያት ናቸው። አንባቢ አንድን ልቦለድ ይዞ ሲያነብ በቅድሚያ የሚጠይቀው ነገር ባለታሪኮቹ እነማን ናቸው? የሚለውን እንጂ የባለታሪኮቹ መቼት እንዴት ነው? ግጭቱስ?ወዘተ.... የሚለውን አይደለም። እነ ዕገሌ ምን ሆኑ? በኃላስ ምን ይሆናሉ?... እንዲህ ቢያደርጉስ ኖሮ? ብሎ በመጠየቅ መልስ የሚያገኝበትና አስተያየት የሚሰጥበት ነው። በመሆኑም የልቦለድ ደራሲ ከሕይወት /ከኑሮ/ ልምዱ የቀሰመውን፣ ያስተዋለውንና የታዘበውን ተሞክሮ ለተደራስያን የሚያቀርበው በምናብ በፈጠራቸው ገፀ-ባህርያት አማካይነት ነው። ገፀ-ባህርያት ለተደራሲው ታሪኩ ሳይዛባ እንዲደርስ መንገድ የሚሆኑ ዋነኛ ማሣሪያዎች ናቸው። ደራሲው ያሰበው ታሪክ ግብ ይመታለት ዘንድ ለገፀ-ባህርያቱ ተገቢ የሆነ ውጫዊና ውስጣዊ ባህሪ ያላብሰቸዋል-አሳማኝ በሆነ መልኩ-ለምን?ቢባል የገሀዱ ዓለም ነፀብራቅ ስለሆኑ። ገፀ-ባህርያቱ የደራሲው ዋናና መሠረታዊ መሣሪያ እንደመሆናቸው ታሪኩ የማነው? ተብሎ ቢጠየቅ የገፀ-ባህርያቱ ነዋ! የሚል ይሆናል። የመኖሪያ ቦታ ተበጅቶላቸው በጊዜ ቅደም ተከተል የሚመላለሱት ገፀ-ባህርያት ናቸው፣ ግጭት ውስጥ የሚገቡትና የሚወጡት እነሱው ናቸው። ስለዚህ የልቦለድ የመሠረት ድንጋይ ገፀ-ባህርያት ናቸው ቢባል ማጋነን አይሆንም። በመሆኑም የዚህ ጥናት አቅራቢ የእነዚህን የገፀ-ባህርያት መውጫ፣ መግቢያ፣ ሕይወት አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባሕሪ፣ ከተመሳስሎና ከዘላቂነት እንዲሁም ከተአማኒነት አንፃር በምዕራፍ ከፋፍሎ ለመተንተን ይሞክራል። በአጠቃላይ የዚህ <u>የከርታታው</u> ልቦለድ ገፀ-ባህርያት አሳሳል ትንተና አራት ያህል መዕራፎችን የያዘ ሲሆን አንደኛው ምዕራፍ ከሌላኛው ምዕራፍ ተያያዥነት ኖሮት መልክ እንዲይዝ የጥናቱ አቅራቢ የተቻለውን ጥረት አድርጓል።

### 1.2 የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

ይህ ልቦለድ መጽሐፍ ታትሞ ለመጀመሪያ ጊዜ እጄ እንደገባና አንብቤ እንደጨረስኩት አንድ ነገር በአእምሮዬ ብልጭ አለ። ጥያቄም አጫረብኝ-ለምን የመመረቂያ ጽሑፌን አልሠራበትም የሚል። ስለምን ቢባል በመጽሐፉ ውስጥ የተሳሉት ገፀ-ባህርያት ለየት ያሉ በመሆናቸው ብዙ ትምህርትና ግንዛቤ ያስጨብጣሉ በሚል ነው። ያም ተሳክቶ የመመረቂያ ርዕስ አቅርቤም ፀደቀልኝ። በዚህም የተነሳ በመጽሐፉ ውስጥ ስለሚገኙት የተወሰኑ ገፀ-ባህርያት አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ ከአሳሳል አንፃር ለማጥናት ወሰንኩኝ። ይህን ጥናት ለማድረግ በእጅጉና በአንደኛነት ያነሳሳኝ ጉዳይ ደግሞ በልቦለዱ ውስጥ የተሳለው ዋና ገፀ-ባህሪ ሙት መንፈስን ወክሎ የቀረበ በመሆኑ ነው። በአገራችን ለመጀመሪያ ጊዜ በገሀዱ አለም በሌላ ገፀ-ባህሪ ላይ የተሰራ ሥራ በ1955 የተደረሰው <u>አልወለድም</u> በአቤ ጉበኛ ነበር። ከዓመታት በኃላ ደግሞ በሙት መንፈስ የተሳለ ገፀ-ባህርይ የሚተረክ <u>ከርታታው</u> ታተመ፤ ስለዚህ ለምን ዲ.ማ.ፅ አልሰራበትም

ብዬ ተነሳሳሁ። ሁለተኛ ያነሳሳኝ ምክንያት በአንዲህ አይነት ገፀ-ባህሪ ዙሪያ የተሰራ ምንም አይነት ጥናታዊ ጽሑፍ ባለማግኘቴ ነው። በመሆኑም በከርታታው ልቦለድ የተሳሉት ገፀ-ባህርያት ውጫዊ መልክና ውስጣዊ ባህሪ እንዴት ነው? ምንስ ይመስላሉ? የገፀ-ባህርያቱ የተመሳሳይነት ጉዳይ እንዴት ይታያል? ግጭቱስ ተአማኒ ነው? አይደለም? ለሚሉትና ለመሳሰሉት ጥያቄዎች መልስ እንዳገኝ ነው በተጠቀሰው መጽሐፍ ዙሪያ ለመሥራት የተነሳሳሁት።

### 1.3 የጥናቱ ዓላማ

ማንኛውም ጥናት አላማ እንዳለው ሁሉ የዚህ ጥናታዊ ጽሑፍም ዋነኛ አላማ እንደሚከተለው ቀርቧል፤

1. የገፀ-ባህርያትን አሳሳል መሠረት ያደረገ ሆኖ ደራሲው ገፀ-ባህርያቱን በተገቢው መንገድ ስሏቸዋል ወይ? የሚለውን ጥያቄ የመመለስ አላማ ያለው መሆኑ፤
2. መጽሐፉ በመጠኑም ቢሆን በእውነተኛ ታሪክ ላይ የተመረኮዘ ድርሰት መሆኑን ደራሲው በማስታወሻቸው ላይ አቅርበዋል። የዚህ ጥናት አጥኚ አላማም በመጽሐፉ ውስጥ ያሉ ገፀ-ባህርያት የተሳሉበትን መንገድ ሰፋና ጠለቅ ባለ መልኩ መተንተን፤
3. ለወደፊቱ ደራስያን እንዲህ ዓይነት ሥራ ይዘው ሲቀርቡ በገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ /በተለይ በገፀ-ባህርያት ተመሳስሎ ዙሪያ/ ከፍተኛ የሆነ ጥንቃቄ ያለው ሥራ እንዲሰሩ ለማድረግ ሆኖ ትምህርትና ግንዛቤ ለማስጨበጥ፤
4. ለወደፊት ልቦለድ ድርሰት ለመፃፍ ለሚነሳሱ ወጣት ደራስያን በገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ ጥንቃቄ እንዲያደርጉ ለማስገንዘብ፤

### 1.4 የጥናቱ ወሰን

ይህ ጥናት ደራሲው በተጠቀሰው መጽሐፍ ውስጥ የአፃፃፍ ቴክኒኩን ተጠቅሞ ገፀ-ባህርያቱን ከአካላዊ መልክ፣ ሕሊናዊ ባህሪ፣ ከዘላቂነትና ከገፀ-ባህርያት ተመሳስሎ ወዘተ… አንፃር እንዴት እንደሳላቸውና እንዳቀረባቸው በመመርመር ትንተና ማድረግ ላይ የተገደበ ነው።

### 1.5 የጥናቱ ዘዴና አደረጃጀት

ጥናቱን ለማካሄድ በመጀመሪያ የተደረገው ልቦለዱን በጥልቀትና በሚገባ አንብቦ የገፀ-ባህርያቱን ማንነት በተገቢው ማወቅና የድርሰቱን ታሪክ አሳጥሮ መፃፍ ነው።

በሁለተኛ ደረጃ እያንዳንዱ ገፀ-ባህሪ እንዴት እንደተሳለ፣ ማንነቱን፣እድገቱን፣ ፖለቲካዊ አቋሙን፣ የትምህርት ደረጃውን፣ አስተሳሰቡን፣ አላማውን፣ ማህበራዊ ተሳትፎውን፣ ለድርሰቱ ወደፊት መሄድ ምን ፋይዳ እንዳመጣ፣ ድክመቱንና ጥንካሬውን ለቅሞ በማውጣት መለየት።

በሶስተኛ ደረጃ በመጀመሪያ ምዕራፍ በጥናቱ ዳራ ሥር መግቢያ በመፃፍ የጥናቱን አነሳሽ ምክንያት፣ የጥናቱን ዓላማ፣ የጥናቱን ወሰንና የጥናቱን ዘዴና አደረጃጀት መፃፍ።

በሁለተኛው ምዕራፍ በክለሳ ድርሳናት ሥር የተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝትንና ትወራዊ ዳራ መመልከት ሲሆን፤ ከዚያም በሶስተኛው ምዕራፍ የከርታታውን ልቦለድ መጽሐፍ በድጋሚ በማንበብና በሚገባ በመረዳት በጥሩ ሁኔታ አፅመ ታሪኩን በመፃፍ በገፀ-ባህርያቶቹ ላይ ትኩረት በማድረግ ስለአካላዊ መልካቸውና ሕሊናዊ ባህርያቸው የሰፈረውን መረጃ በማስታወሻ ለቅሞ በማውጣት ለትንታኔ ዝግጁ ማድረግ፡፡ ከዛም በመቀጠል በካርድ የተሰበሰቡትን መረጃዎች / Data / እንደገና በማጥናትና ለትንታኔው የተሻለ ማሳያ የሆኑትን በመምረጥ ወደ ዋናው ትንተኔ መግባት፡፡

በመጨረሻም ማጠቃለያ፣ ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸውና ዋቢ ጽሑፎች አቅርቦ ማጠቃለል፡፡

## ምዕራፍ ሁለት

## ክለሳ ድርሳን

### 2.1 የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝት

የተለያዩ ልቦለዶችን ለጥናት የመረጡ ተማሪዎች በገፀ-ባህርያት ዙሪያ ጥናት ለማካሄድ መንደርደሪያ ይሆናቸው ዘንድ የተለያዩ የጥናት ወረቀቶችን እየመረጡ ጠለቅ ያለ ዳሰሳ አርገዋል፡፡ከዛም በመነሳሳት የመመረቂያ ስራቸውን ሰርተዋል፡፡ከነዚህም መካከል ከእኔ ጥናት ጋር ይዛመዳሉ በምላቸው በተወሰኑት የጥናት ስራዎች ላይ ቅኝት አድርጌአለሁ፡፡በፍለጋውም ወቅት በከርታታው ልቦለድ ድርሰት ላይ አንድም ጥናት አልተካሄደም፤ነገር ግን በሌሎች ልቦለዶች ላይ በተመሳሳይ የጥናት ርዕስ የተሰሩ ብዙ የተዛማጅ ጥናቶች አሉ፡፡

ከሰበሰብኳቸው በርካታ ጥናታዊ ጽሑፎች አብዛኛዎቹ አጥኚዎች በመረጧቸው መጽሐፍት የገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ ላቅ ያለ ትንተና ሰጥተዋል፡፡እኔም በገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ የተጠኑ ሶስት ያህል ጥናቶችን አግኝቻለሁ፡፡ጥናቴም በጣም ይቀራረባሉ ባልኳቸው በእነዚህ በሶስቱ ላይ ያተኩራል፡፡ እነዚህ ጥናታዊ ጽሑፎችም ሙሉ በሙሉ ባይሆንም የገፀ-ባህርያት አሳሳል ትንተና ለማካሄድ መሰረት ባደረጓቸው አንድአንድ ነጥቦች ውስጥ ከኔ ጥናት ጋር ይዛመዳሉ፡፡የኔ ጥናት ከነዚህ ጥናቶች ጋር በመሰረታዊነት የሚለየው ልቦለድ ድርሰቱ አዲስ መሆኑና እስከአሁንም ምንም አይነት ጥናት ያልተሰራበት መሆኑ ነው፡፡

በዚህ ጥናት ከሚዳሰሱት ተዛማጅ ጥናቶች መካከል በመጀመሪያ የታየው የአፀደ ማሩ “የገፀ-ባህርያት አቀራረፀ በየምሽት እንግዳ ረጅም ልቦለድ” በሚል ርዕስ በ1996 ያቀረበችው የመመረቂያ ጽሑፍ ነው፡፡ አጥኚዋ ጥናቷን በአራት ምዕራፎች የከፋፈለች ሲሆን፤ጥናቷ ያተኮረው በምዕራፍ ሦስት በልቦለዱ የገፀ-ባህርያት አቀራረፀ ትንተና በመስጠት ላይ ነው፡፡በዚህ ምዕራፍ በመጀመሪያ የልቦለዱን አፅመ ታሪክ በመፃፍ ከዛ ወደ

ትንታኔ አምርታለች፡፡ በቀጠልም በልቦለዱ ውስጥ ያሉትን አስፈላጊ የተባሉ ገፀባ-ህርያት ለይታ በማውጣት ያላቸውን ውጫዊ መልክና ውስጣዊ ባህሪ በመተንተን አሳይታለች፡፡ እንዲሁም ገፀባ-ህርያቱን ከዘላቂነትና ከተአማኒነት አንፃር አይታለች፡፡ ልቦለዱ ከዘላቂነትና ከተአማኒነት አኳያ ያለበትን ችግርም ከልቦለዱ ምሳሌ በመጥቀስ ለማሳየት ሞክራለች፡፡ በዚህም ልቦለዱ ከዘላቂነትና ከተአማኒነት አንፃር ደካማ መሆኑን ገልፃ አልፋለች፡፡ይህም ከኔ ጥናት ጋር አንድ ያደርጋታል፡፡

አንድ አጥኚ ጥናት በሚያጠናበት ጊዜ የተሰሩ የጥናት ወረቀቶችን (ጽሑፎችን) ከሱ ጥናት ጋር ያለውን አንድነትና ልዩነት መፃፍ ብቻ ሳይሆን የዛን ጥናትም ድክመትና ጥንካሬ ማስቀመጥ አለበት፡፡ የአጥኚዋም (አፀደ) ችግር በመሰረታዊነት ጥ ናቷን በገፀ-ባህርያት አካላዊ መልክ እና ውስጣዊ ባህሪ ላይ፣ በተአማኒነትና በዘላቂነት ላይ ብቻ ማተኮሯ ነው፡፡ ነገር ግን በገፀ-ባህርያት ላይ ጥናት ሲደረግ በነዚህ ጉዳዩች ላይ ብቻ ማተኮር ጥናቱን ሙሉ አያደርገውም፡፡አንድ ልቦለድ ሲጠና ከብዙ አቅጣጫዎች ቢጠና ይመረጣል-የጥናት ገደቡ እስከፈቀደ ድረሰ፡፡ ለምሳሌ ገፀ-ባህርያቶቹን ከመቼት፣ ከግጭት.....ጋር ያላቸውን ጥምረት (ቁርኝት) ተንትኖና በትኖ መግለፀ ይገባል፡፡ምክንያቱም ገፀ*ባህርያት የሚሳሉት ከመቼት፣ከግጭት...በመነሳት ጭምርም ነውና፡፡የኔ ጥናት ግን በመጠኑም ቢሆን ገፀ-ባህርያትን ከግጭት አኳያ ለማየት በመሞከሩ ከዚህ ጥናት ጋር ሲተያይ ለየት ያደርገዋል፡፡አጥኚዋ በገፀ-ባህርያት ውጫዊ መልክ፣ውስጣዊ ባህሪ፣ ከዘላቂነትና ከተአማኒነት አንፃር ጠልቃ በማየቷ የጥናቷን ጥንካሬ ያሳያል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ ከዚህ ጥናታዊ ጽሑፍ ጋር ተመሳስሎ ያለው መሰሉ መንግስቱ “የገፀ-ባህርያት አሳሳል ብልሃት በሲሳይ ንጉሱ” በሚል ርዕስ በ1986 ያቀረበችው የመመረቂያ ጽሑፍ ነው፡፡አጥኚዋ የደራሲውን ሶስት ስራዎች የሰመመንን፣የግርዶሽንና የትንሳኤን ልቦለዶች የገፀ-ባህርያት አሳሳል በማየት በጥልቀት ተንተናለች፡፡ሶስቱን ልቦለዶች ብልሀት በተሞላበት ሁኔታ የገፀ-ባህርያቱን አቀራረፅ አነፃፅራ ለማየት ሞክራለች፡፡ጥናቱ ከተደረገበት የዘመን ርቀት አንፃር ጠንከር ያለ ሥራ ማቅረቧ የሚደነቅ ነው፡፡የመሰሉ ጥናት ከኔ ጥናት ጋር የሚለየው የሷ ጥናት በሶስት ልብለዶች ላይ ማተኮሯ ጥናቷን ሰፊ ማረጉ ነው፡፡ሌላው ልየነቱ ደግሞ በአፀደ ማሩ እደታየው ጥናት ሁሉ የመሰሉም ጥናት ገፀ-ባህርያትን ከመቼትና ከግጭት.....አንፃር ያላቸውን ጥምረት አለማሳየቷ ነው፡፡ ተመሳስሏችን ግን የኔም ሆነ የሷ ጥናት በገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ ማተኮሩ ነው፡፡

ሌላው የመሰሉን ጥናት እጅግ ሙሉ የሆነ ጥናት የሚያደርገው የመጽሐፎቹን ደራሲ የሲሳይ ንጉሱን ታሪክ ቅልብጭ ባለ መልኩ ማቅረቧና አጠቃሎ መፀፋ ነው፡፡

መሰሉ በሶስቱም ድርሰቶች ውስጥ ደራሲው የተጠቀመበት የአሳሳል ብልሀት ድክመቶች የጉሉ መሆናቸውን አሳይታለች፡፡ ከድክመቶቹ ውስጥም ገፀ-ባህርያቱን

በተዘዋዋሪ መንገድ መሳል ከጀመረ በኃል መልሶ ለተራኪው ይሰጠዋል፡፡ገፀ-ባህርያቱን ፍፁማዊነት ስላላበሳቸውም ተአማኒነትን አጉድለዋል፡፡ ገፀ-ባህርያቱ በንግግር ያሉትን ተራኪው በመድገሙም ልብ ሰቀላውን የረገበ አድርጓል ብላለች፡፡ ገፀ-ባህርያትን በቋንቋ በሚስልበት ጊዜ ዘይቤአዊ አነጋገር አለመጠቀሙና አንድ ገፀ-ባህሪ ከሌላው ገፀ-ባህሪና ከተራኪው የሚለይበት ቃላት አመለጠቀሙ ማን ምን አለ የሚለው ተለይቶ እንዳይታወቅ ከማረጉም በላይ የደራሲው የቋንቋ አጠቃቀም ደረቅና ተራ ቃላት የታጨበት ነው ስትል ሂሳለች፡፡ የድርሰቱ ዋና ገፀ-ባህርያት ራሳቸውን ወክለው መንቀሳቀስ ያቃታቸውና በሌሎች ረዳትነት ሲታገዙ መታየታቸው ለድርሰቱ ድክመት ዋናኛው ነው በማለት አስተያየት ሰጥታለች፡፡

ደራሲ ሲሳይ ንጉሱ በሦስቱም ድርሰቶች ተመሳሳይነት ያላቸውን የገፀ-ባህርይ አሳሳል ዘዴዎችን የተጠቀመ በመሆኑ አንዱ ከአንዱ ራሳቸውን ችለው ተለይተው እንዲታወቁ አላደረገም ስትልም አስተያየት ሰጥታለች፡፡አጥኚዋ እንዳለችው ከላይ የጠቀስናቸው ችግሮች በልቦለድ መንፀባረቃቸው እንዳለ ሆኖ ሕሊናዊ መልክ አሳሳሉ ግን ጠንካራ ሊባል የሚገባ መሆኑን በመጥቀስ ጥናቷን አጠቃላለች፡፡

በሶስትኛና በመጨረሻም ከዚህ ጥናት ጋር ተመሳሳይነት ያለው ሥራ "የቋንቋ አጠቃቀምና የገፀ-ባህሪ አቀራረፅ በሚክሎል የመቻል ሚዛን" በሚል ርዕስ ራሔል ኢታና፣ በ1995 ዓ.ም ያቀረበችው ጥናታዊ ጽሑፍ ነው፡፡ አጥኚዋ ጥናቷን በሶስት ምዕራፎች ከፋፍላ ለማየት ሞክራለች፡፡ በምዕራፍ አንድ የጥናቱ አላማ፣የጥናቱ ገደብ፣የጥናቱ ጠቀሜታ፣የአጠናን ዘዴ፣የተዛማጅ ጥናቶች ቅኝትና አፅመ ታሪክ ሲሆን፤በምዕራፍ ሁለት ከኔ ጥናት ጋር ፈፅሞ ተዛማጅነት የሌለው የቋንቋ አጠቃቀም ተካቷል፡፡በምዕራፍ ሶስት የገፀ-ባህርያት አቀራረፅን በገለፃ፣በንግግርና በድርጊት በሚሉ ንዑሳን ርዕሶች አቅርባለች፡፡

አሁንም በዚህ በሶስተኛው ጥናታዊ ጽሑፍ ላይ አለ ብዬ የማምነው የአጠናን ድክመት አጥኚዋ ገፀ-ባህርያቱን ከግጭት፣ከመቼት…አንፃር ምን እንደሚመስሉ አለማየቷ ነው፡፡ይህም ሌላው የእኔና የሷ ጥናት የሚለይበት ሆኖ አግኝቼዋለሁ፡፡የአጥኚዋ ስራ ከጥንካሬ አንፃር ሲታይ ግን የገፀ-ባህርያት አቀራረፅን በገለፃ፣በንግግርና በድርጊት መንገድ በሚል ንዑሳን ርዕሶች ከፋፍላ በማጥናቷ ግሩም የሚያሰኝ ስራ አሳይታለች፡፡

አጥኚዋ በምዕራፍ ሶስት የገፀ-ባህርይን አቀራረፅ በመቃኘቷ ከኔ ጥናት ጋር ተመሳሳይ የሆነ ጉዳይ አለን፡፡ራሔል አንድ ዋና ገፀ-ባህሪን በመውሰድ ህሊናዊና አካላዊ መልኩ በገለፃ እንዴት እንደቀረበ አሳይታለች፡፡ በተጨማሪም ገፀ-ባህሪው በታሪኩ ውስጥ ያለው እንቅስቃሴ በንግግር በድርጊት እንዴት እንደተሳለ አይታለች፡፡

ራሔል በመጨረሻም ጥናቷን ስታጠቃልል ደራሲው ገለፃን ተጠቅሞ የሳለው የዋናው ገፀ-ባህሪ አካላዊ መልክ ደካማ ነው ብላለች ይህም ከኔ ጥናት ጋር ያመሳስለዋል፡፡ አካላዊ መልኩን የሚያሳይ ነገር በጉልህ አልተጠቀመም ብላለች፡፡በሌላ በኩል ንግግርና

ድርጊትን በተመለከተ የገፀ-ባህሪውን እምነት፣ምኞች፣ተስፋና አላማ አሳይቷል፡፡በዚህ ረገድም ገፀ-ባህሪውን በጥሩ ሁኔታ ቀርፆታል በማለት ግላዊ አመለካከቷን በማስቀመጥ አጠቃላለች፡፡

በመጨረሻም ሌላው የእነዚህ ሶስቱ የተዛማጅ ፅሁፎች ዋና ድክመት አሁን ባሉ በደራሲያን ዘንድ መሰረታዊ ውጤት አለማምጣታቸው ነው፡፡ በአሁኑ ዘመን ያሉ ደራሲዎች-በተለይ እኔ የመረጥኩትን ልቦለድ የፃፉት ደራሲ ወይ ጥናቱን አላዩትም አይተውም ከሆነ ጥናቱ ምንም ውጤት አላመጣላቸውም ባይ ነኝ፡፡ምክንያቱም የጥናት ስራዎች ደራሲያንን ድርሰት በሚፅፉበት ጊዜ ስህተት እንዳይፈጽሙ የሚያስተምሩ ስለሆነ፡፡ውጤታቸውም ጥሩና የተዋጣለት የድርሰት ስራ ማውጣት ስለሆነ፡፡ስለዚህ ማናቸውም ደራሲያን ድርሰት የመፃፍ ክህሎት ቢኖራቸውም እንኳን በከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በዘርፉ የተሰሩ ጥናቶችን በቅድሚያ ማየት ይጠቅባቸዋል ብዬ እመክራሁ፡፡

## ምዕራፍ ሦስት

### 3. የገፀ-ባህርያት አሳሳል በከርታታው ልብወለድ

### 3.1 የከርታታው ልብ-ወለድ ታሪክ በአጭሩ

የዚህ መፅሀፍ ታሪክ የሚጀምረው አያልቅበት የተባለው የዚህ መፅ ሀፍ ተራኪ በተኛበት በእኩለሊት ስድስት ሰዓት ከሀምሳ ላይ ነው፡፡ ስልኩ በድንገት ይጮህና ያነሳዋል ከወዲያኛው የስልክ መነጋገሪያ የከርታታው ሰራተ ኛ የሆነችውን የቤዛን ድምፅ ይሰማል፡፡ ምን እንደሆነችም ሲጠይቃት ከርታታው በጠና መታመሙን ትነግረዋለች፡፡

ከዛም በፍጥነት እንቅልፉ ይነሳና ወደከርታታው ቤት በማምራት ከርታታውን የሁለቱም ወዳጅ ወደሆነው ሐኪም ፣ ዶ/ር በለው ዘንድ ይወስደዋል ፡፡

ዶ/ሩም ከርታታውን ከመረመረ በኃላ በመጠጥ ብዙ እንደተጎዳ ፤ ያለው እድል የመነመነና ሊተርፍእንደማይችል ለአያልቅበት በሀዘኔታ ይነግረዋል፡፡ ከጥቂት ቀናት በኋላም ከርታታው ብዙ ተሰቃይቶ ከዚህ ዓለም በሞት ይለያል፡፡ የቀብር ሥር ዓቱም በቅዱስ ዮሴፍ ቤተክርስቲያን ይከናወናል፡፡

ታሪኩ በዚህ እየቀጠለ የከርታታው ሙት መንፈስ ለአያልቅበት ይገለፅለታል፡፡ ስለብዙ ጉዳዮችም ያወያየዋል- በተለይ ድብቅ ስለሆነው የሕይወት ታሪኩ ይነግረዋል . . . አብረው ካደጉበት ጨፋ - ስሬ ከሚባል ፁ ከአንዲት ፀሀይ ከምትባል ልጃገረድ ጋር የከንፈር ወዳጅነት ጀምሮ እንደነበረና በኋላ ላይም ሁለቱም ተሳስተው መፀነሷን ፤ ከዚያም በባህላዊ መንገድ ፅንሱን እንድታስወጣው ቢጠይቃት እምቢ ማለቷን፡፡ . . . ከዚያም ይህ ጉዳይ ለሕይወቱ ስለሚያሰጋው ጥሏት ወደ አዲስ አበባ መጥፋቱን ይነግረዋል፡፡ ከዚያ በኋላ ግን የሆነውን ሁሉ በውል እንደማያውቅና ይህን ሚስጥ ሩን ግን አሁን በሕይወት ያለው አብሮ አደጉ ወደመንደሩ ሄዶ እንዲያረጋግጥለትና ፀሀይና ልጁ እንዲሁም ወላጅ እናቱ በህይወት ካሉ ሁሉንምእርስ በእርስ እንዲያስተዋውቅለት ቃል ያስገባውና ይሰወራል፡፡

ይህን የሙት ቃል ከግቡ ለማድረስ አያልቅበት ለሁለቱም የቅርብ ወዳጅ ለሆነው ለአለበል ዘርዝሮ ይነግረዋል፡፡ አለበልም የሙት መንፈስን ለማመን ትንሽ ቢያቅማማም በመጨረሻ አምኖ ለጉዞ ተዘጋጅተው ወደ አውቶብስ ተራ ያቀናሉ፡፡ አውቶብስ ተራም ደርሰው ትንሽ የእቃ ጫኝና አውራጆች ችግር ቢገጥማቸውም ጨቡዴ በሚባል የአካባቢው ተሸካሚ ነገሮችን አቅልሎላቸው አውቶብስ ተሳፍረው ወደ ደሴ ይሄዳሉ፡፡

ከዚያም ወለዲ ደርሰው ምግብ አዘው ከበሉ በኋላ አለበል በጠቋሚሟል፡፡ አለበል እዚያው በመቅረት ለመታከም ይስማሙና አያልቅበት ጉዞውን ይቀጥላል፡፡ ከጥቂት ሰዓታት በኋላም አያልቅበት ወደከርታታው ትውልድ ስፍራ ይደርሳል፡፡ አብዬ ሀምዛ ከሚባሉ የአካባቢው ሽማግሌ ቤትም ያርፋል፡፡

ከሰዓታት በኋላ የአብዬ ሀምዛ ልጅ የሆነው ፈለቀ፤ የፈለቀ ጓደኛ በላይና ዘነበች አብዬ ሀምዛን ለመጠየቅ ፎቻቸው ይደርሳሉ፡፡ ሁሉም ከአያልቅበትና አብዬ ሀምዛ ጋር ሰላምታ ይለዋወጡና ከቤት አረፍ እንዳሉ - አያልቅበት ከአዲስ አበባ የመጣበትን ጉዳይ ይነግራቸዋል፡፡ በከፎታው ሁኔታም እጅግ በማዘን አደራውን ለመወጣት ቃል ተገባብተው ሁሉም ወደየመኝታቸው ያመራሉ፡፡

በነጋታው ጉዳዩን ፈር ለማስያዝ ወደየፊናቸው ይሰማራሉ፡፡ ዘነበች በአንድ በኩል ስለከርታታው የከንፈር ወዳጅ ስለፀሀይ ለማወቅ ድሮ ወደምታውቃቸው ወ/ሮ ሸዋዬ አመራች፡፡ ታሪኩንም ከወ/ሮ ጀማነሽ እንደምታገኝ ወ/ሮ ሸዋዬ ነግረዋት ትመለሳለች፡፡

በሌላ በኩል ደግሞእነአያልቅበት ነፍሴ ከሚባል ገበያ ወጥተው ገበያተ ኛውን ስለከርታታው የከንፈር ወዳጅ ስለፀሀይ የሚያውቅ ሰው እንዳለ ለማጣራት ሄዱ፤ ነገር ግን ምንም ፍንጭ ሳያገኙ አለበልን አግኝተው ተመለሱ፡፡

በንጋታው ጠዋት የዘነበችን መረጃ በመያዝ አያልቅበት፣አለበልና ፈለቀ በመሆን የፀሀይ እናት ወ/ሮ አሰገደች ሚስጥረኛ የሆኑትን ወ/ሮ ጀማነሽን ለማነጋገር ስሬ ወረዱ፡፡ ወ/ሮ ጀማነሽም ምንም ሳየሳፍሯቸው የፀሀይእናት ወ/ሮ አሰገደች የነገሯቸውን ሚስጥር በሙሉ ነገሯቸው፡፡

የፀሀይ እ ናትም ፀሀይ ከጋብቻ ውጪ በማርገዟ የተነሳ ክብሬ ተነካ በማለትና የአካባቢውን ባህል በመፍራት ፀሀይን ዘጠኝ ወር ሎቤት ይሸሽጋሉ፡፡ በኋላም ስትወልድ በአካባቢው ልጅ መውለድ ያቃት ትእግስት ከምትባል መሀን ሴት የፀሀይን ልጅ ይሰጣሉ፡፡ እነአያልቅበትም ይሄን ሚስጥር በመያዝ ቀጥታ ወደነ ትዕግስት /መሀኗ/ ቤት በመሄድ የፀሀይ ልጅ የሷ ልጅ አለመሆኗንእንደደረሱበ ት ይነግሯታል፡፡ ልጅቱም የከርታታውና የፀሀይ መሆኗን ያስረዷታል፡፡ ይህን ታሪክ በተመሳሳይ መልኩ ለከርታተው እናት ወ/ሮ አዋጋሽ ይነግራሉ፡፡ ልጃቸው ዘሩን ትቶ መሞቱ ይህንንም አደራለመወጣት አዲስ አበባ ድረስእንደመጡ ጨምረው ይናገራሉ፡፡ ስለዚህ የከርታተው የከንፈር ወዳጅ የሆነቻው ፀሀይ ፣ የከርታታው ልጅን እና የከርታታውን እናት እርስ በእርስ ለማስተዋወቅ በከርታታው እናት ቤት እንዲገናኙ ተቀጣጥረው ይለያያሉ፡፡

በማግስቱ ሁሉም በከርቻታው እናት ቤት ተገናኝተው የከርታታውን ልጅ ትንግርትን ለስጋ ወላጅእናቷ ለፀሀይ እና ለከርታታው እናት አስተዋወቁ፡፡ የከርታታው እናትም በነገሩ ተደሰቱ፡፡ በመጨረሻም የከርታታው ሙት መንፈስ በተሰበሰቡበት ተገልፆ

ፀሀይን መበደሉንና እናቱን ማስቀየሙን ተናዞ ይቅርታ ጠይቆ ይሰወራል፡፡ ታሪኩም በዚህ ያበቃል፡፡

### 3.2 የከርታታው ልቦለድ ገፀ-ባህርያት አሳሳል ትንተና

#### 3.2.1 አያለቅበት አለሙ

አያልቅበት አለሙ ይህን ከርታታው የተሰኘውን ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ በአንደኛ መደብ ነጠላ / እኔ ባይ/ አተራረክ የሚተርክ ነው፡፡ የልቦለዱን ፍሰት ተከትሎ-በእያንዳዱ የመታጠፊያ መንገዶች ላይ አብሮ እየተጓዘ ፣ አቅጣጫ እያመለከተና ለተደራስያኑ የልቦለዱን ታሪክ ከታሪኩ ጋር አብሮ እየኖረ እና ድርጊቶችን እየከወነ የሚያሳይ ዋና ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ የዚህን የታሪኩ ዋነኛ አካል የሆነውን ገፀ-ባህሪ አካላዊ መልክና ህሊናዊ ባህሪ መጽሐፉን ውስጥ በተገኘው መረጃ እና ደራሲው በቴክኒካዊ መልኩ ባሳየው አፃፃፍ ስልት በመመስረት እንዲህ ተስሎ እናገኘዋለን፡፡

##### 3.2.1.1 የአያልቅበት አለሙ አካላዊ መልክ

በዚህ ከርታታው በተባለው ረጅም ልቦለድ ድርሰት ውስጥ በዋና ገፀ-ባህሪነት የተሳለውና የልቦለዱን ሽክርክሪት / መሪ/ እንዲይዝ የተደረገው አያልቅበት አለሙ ነው፡፡ የአካላዊ መልኩ አገላለፅ ከአንድ ረጅም ልብወለድ በማይጠበቅ መልኩ በበቂ ሁኔታ ሳይገለፅና ተደራሲው ልብ ውስጥ ሳይሳል /ግዝፍ ሳይነሳ/ እንዲሁ በግርድፉ ተስሎ ይታያል፡፡ በመሆኑም የገፀ-ባህሪውን አካላዊ መልክ ለማወቅና ምናብ ለመሳል የፈለገ አንባቢ /ተደራሲ/ እስከ ገፅ 144 ድረስ /የመጽሐፉን አጋማሽ ድረስ ሊባል በሚችል መልኩ/ ቢለፋና ቢጥር የአያልቅበትን ውስጣዊ ባህሪ እንጂ አካላዊ መልኩን የማወቅ ምንም ዕድል በደራሲው አልተሰጠውም፡፡ይህ ደግሞ በተደራሲው ዘንድ አያልቅበት የተባለው ገፀ-ባህሪ በመጽሐፉ ውስጥ እስትንፋስ ያለውና ሥጋ ለባሽ ለመሆኑ ያጠራጥራል፡፡ ምክንያቱም ምንም የተገለፀ አካላዊ መልክ ባለመኖሩ፡፡ ተደራሲው በገሀዱ ዓለም ከሚያውቃቸው ሥጋ ለባሽ ሰዎች መካከል በየትኛው ይመስለው? ጥያቄ ያስነሳል፡፡ ነገር ግን አያልቅበት አሰልቺ የሆነውን ጉዞ ተጉዞ ከአብዬ ሃምዛ ጋር ሲገናኝና ፣ አብዬ ሀምዛም በልጃቸው በፈለቀ በኩል አስታከው ኢ-ርቱዕ በሆነ መልኩ የሚከተለውን ሲናገሩ የአያልቅበትን ያለዕድሜ መሽምገልና መመለጥ አንባቢው ይረዳል፡፡ “ አዬ አያልቅበት ! እንዳንተው ያለ ዕድሜው የሽምግለና መልክ አምጥቷል፡፡” አሉ ሂብዬ ሀምዛ አባባላቸው እሱም እንዳንተው መላጣ ሆኗል ማለታቸው እንደሆነ ገብቶታል.“/ ከርታታው ገፅ፥144/

ይህም የአካላዊ መልክ ገለፃ ሙሉ ለሙሉ የተሟላ ነው ለማለት የማያስደፍር እንደሆነ ለማንም አንባቢ ግልፅ ነው፡፡ የሆነው ሆኖ የአያልቅበትን ቁመት መርዘም ፣ ማጠር፣ መወፈር እና መክሳት የመልኩን ቀይነት፣ጠይምነትና ጥቁርነት እዲያውቅ ዕድል ያልተሰጠው አንባቢ የአያልቅበትን መላጣነትና ያለዕድሜው ማርጀት ከላይ በተገለፀው ንግግር ይገለፅለታል፡፡

የአያልቅበትን የመልክ ከለር ለማወቅ ወይም ለመገመት የፈለገ አንባቢ አያልቅበት ከወ/ሮ ጆማነሽ / የከርታታው የከንፈር ወዳጅ /የፀሀይ እናት ጓደኛ/ ጋር ያደረገውን ንግግር ተመርኩዞ አያልቅበት ቀይ ነው ወደሚል ድምዳሜ ሊደርስ ይችላል፡፡

"....... ታዛዥ አያሳጣህ እያሉ ይመርቁኝ የነበርኩት አያለቅበት ነኝየሚጠሩኝ 'ቢጫ' እያሉ ነበር...."/ከርታታው ፥ 246/

እኚህ ሴት አያልቅበትን 'ቢጫ' እያሉ ይጠሩት ከነበረ አያልቅበት 'ቀይ' ነበር ብሎ አንባቢ ሊገምት አሊያም ሊጠረጥር ይችላል፡፡

ይህም ሁሉ ሆኖ ግን አያልቅበት ዋና ገፀ-ባህሪ የመሆኑን ያህል ተገቢ በሆነ ወይም በቂና አሳማኝ በሆነ መልኩ በዕርቱዕ ወይም በኢ-ርዕቱዕ የገፀ-ባህርያት አቀራረብ ዘዴዎች አካላዊ መልኩ አልተሳለም፤ወይም አልተሟላም ለማለት ይችላል፡፡ ይህም ገፀ-ባህሪው በተደራሲው ልቦና ውስጥ ተገቢ የሆነውን ስዕል ይዞ /ግዝፍ ነስቶ/ እንዳይኖር የራሱ የሆነ ትልቅ ተፅህዕኖ ትቶ አልፏል፡፡ የሆነ ሆኖ አያልቅበት ለምን ይህን ሁሉ ገፅ /144 ገፅ/ ድረስ ተደራሲው ህሊናዊ ባህሪውን እንጂ አካላዊ መልኩን እንዳያውቅ ተደረገ ? የሆነ የአፃፃፍ ቴክኒክ በመጽሐፉ ይኖር ይሆን? የሚሉትን ጥያቄዎች ለመመለስ ወደ ትንተናው ስመለስ ይህን አገኛለሁ፡፡

የአያልቅበት የአካላዊ መልክ ገለፃ እስከ ገፅ 144 ድረስ በድርሰቱ ውስጥ አለመታየቱ ልቦለድ መጽሐፉ ካሳየን ወጣ ያለ የመለክ ገለፃ ቴክኒክ አኳያ ሊሆን ይችላል፡ ፡ የድርሰቱ የአፃፃፍ ቴክኒክ ተደራሲው አያልቅበት የተባለውን ገፀ-ባህሪ ምን አይነት ሰው ነው? ብሎ በመጠየቅ መልሱንም በጉጉት እንዲጠብቅ ከማድረግ አንፃር ይሆናል፡፡ ብዙ ጊዜ በአንደኛ መደብ የትረካ አንፃር እኔ እያለ የሚተርክ ልቦለድ የደራሲውን የግል አስተያየትና የሕይወት ፍልስፍና እንዲሁም ማንነት በጉልህ የሚንፀባረቅበት ነው፤ በመሆኑም በመጽሐፉ መጨረሻ /ጀርባ/ ላይ የሚገኝ የደራሲው ፎቶ ስላለ የአካል ገለፃው ምን ይረባል ከሚል አመለካከት የመነጨ ሊሆን ይችላል፡፡ ያም አንድ አዋጭ ምክንያት በመሆን የአካል ገለፃው ላይ ብዙም እነዳያተኩርበት ያረገው ይሆናል፡፡ የአያልቅበት አካላዊ ማንነት ምን ይመስላል? ለሚለው  የተደራሲያን ጥያቄ መልሱ በጀርባ /በመፅሀፉ መጨረሻ/ያለው የደራሲው ፎቶ ነው ወደሚል አዲስ ቴክኒክ ያዘነበለ ይመስላል፡፡

ይህም እስከ ገፀ 144 የዘለቀው የአንባቢ አያልቅበት ምን አይነት አካላዊ መልክ አለው ጥያቄ ልክ ፎቶውን የመሰለ የአካላዊ መልክ ገለፃ በገፅ 144 ላይ ያገኛል፡፡

".... አባባላቸው እሱም እንዳንተው መላጣ ሆኗል ማለታቸው እንደሆነ ገብቶኛል፡፡"/ ከርታታው ፥ 144/

'መላጣ' የሚለው ቃል የገፀ-ባህሪውን የፊት የመልክ ሁኔታ ከደራሲው ፎቶ ጋር በማነፃፀር አንባቢው ይረዳል፡፡ እስከ ገፅ 144 የመልክ ገለፃን ለሚጠብቅ አንባቢ በአንደኛ

መደብ ለሚተረኩ ድርሰቶች የመልክ ገለፃን በተዘዋዋሪ በደራሲው የመጽሐፍ ጀርባ ፎቶ ማወቅ ይቻላል የሚል መልስ ያስገኝለታል፡፡

ከዚህ ገፅ በኃላ ግን ከፊቱ ከለር ውጪ ምንም አይነት የአካል ገለፃ አልመጣም፡፡ የቁመቱን መርዘምና ማጠር፣የሰውነቱን መወፈርና መክሳት ተደራሲ አያውቅም፡፡ ይህም የልቦለዱን ድክመት ቁልጭ አርጐ ያሳያል፡፡ የአያልቅበትን የፊት መልክ በመጽሐፉ ጀርባ ባለው ፎቶ የመግለፅ የገለፃ ቴክኒኩ የሚደነቅ ሆኖ ሳለ በአጠቃላይ ግን ደራሲው የአያልቅበትን ሙሉ የገፅ ምስል ፈጥሮ የማሳየት ሀይሉ ደካማ ነው ወደሚል ድምዳሜ ያደረሳል፡፡

ስለዚህ የአያለቅበት የመልክ ገለፃን በዚህ አይነት ረጅም የገፅ ብዛት አለመጠቀሱ ተደራስያን ላይ ይህ ነው የሚባል ጥያቄ የሚያስነሳ ሳይሆን የአፃፃፍ ቴክኒኩን መረዳት ጥሩ ነው፡፡

**3.2.1.2 የአያልቅበት አለሙ ውስጣዊ ባህሪ**

አንድን ገፀ-ባህሪ ያለአንዳች አላማ፣ያለአንዳች ግብ ቀርፆና ነብስ ዘርቶ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ እንዲገኝ ለማረግ መሞከር ችግኝን ገልብጦ እንደ መትከል ሊቆጠር ይችላል፡፡ በመሆኑም የከርታታው ልቦለድ ደራሲም አብዛኞዎቹን ገፀ-ባህርያት ያለምንም ግብ ቢቀርጻቸውም አያልቅበት የተባለውን ዋና ገፀ-ባህሪ ግን የድርሰቱ መንሸራሸሪያና መረማመጃ አድርጐ ስሎታል፡፡ ማንኛውም የልቦለዱ የታሪክ ፍሰት በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ መልኩ በአያልቅበት የኑሮ መንገድ ውስጥ ወይም የአኗኗር መስመር ውስጥ እየተከሰተ እንዲከወን የራሱ የሆነ ቴክኒክ ፈጥሮ ከውኖታል፡፡

በዚህ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ አያልቅበት ከሌለ ታሪኩን የምናውቀበት ምንም ዓይነት እድል የለንም፡፡ በልቦለድ ውስጥ ያሉትን ከግማሽ በላይ ገፀ-ባህርያት አውጥተን ልቦለዱን እንወቀው ቢባል ትንሽ ቢከብድም ያስችላል፡፡ አያልቅበት ከሌለ ግን ታሪኩን በምንም አይነት መልኩ ስለማናውቀው ደራሲው አያልቅበት አለሙ የተሰኘውን ገፀ-ባህሪ ወደ ዋናው ታሪክ የሚወስደን፣የሚያደርሰን ብቸኛና ተመራጭ መንገድ አድርጐ ስሎታል /ቀርጾታል/ ምንም እንኳን የልቦለድ ታሪኩን የጭብጥ ሀያልነት ምን ያህል እንደሆነ ለመናገርና በድፍረት ሂስ ለመስጠት ይህ ርዕስም ሆነ መነሻ ስለማይፈቅድልኝ አያልቅበት የተሰኘው ገፀ-ባህሪ ለልቦለዱ ፍሰት አይነተኛ ሚና ተጫውቷል ወይ? ለሚለው ጥያቄ አዎን በሚገባ ተጫውቶታል! የሚል መልስ ከቃለ አጋኖ ጋር ጭምር አንባቢው ሊመልስ ይችላል፡፡ "አንድ ገፀ-ባህሪ ሳቢነት የሚኖረው ቀስ በቀስ እየተገለጠ በሂደት ሲታይ ነው ፡፡" /ዘሪሁን ፥ 168/

ይህን የምሁራን አባባል በአያልቅበት የልቦለድ ኑሮ ውስጥ ስላገኘነው ደራሲው የአያልቅበትን ሕሊናዊ ባህሪ የሳለበት መንገድ ከሌሎቹ በመጠኑም ቢሆን የተሻለ ሆኖ ታይቷል፡፡

አንድ ደራሲ አንድን ልቦለድ ሲፅፍ በወሰነበትና በተነሳበት ሰዓት ከሚፅፈው ታሪክ፣ጭብጥ፣መቼት… እኩል በሆነ መልኩ የገፀ-ባህርያቱን ህሊናዊ ባህሪም ሆነ አካላዊ መልክ በጣም ተጠንቅቆና ጠንቅቆ ሊያውቅ ይገባል፡፡ ያለበለዚያ ግን 'ሽለላው ቢያልቅበት ቀረርቶ ጨመረበት' የሚለው የአገሬ ቢህል ይከተላል፡፡

በመጀመሪያ ደረጃ ገፀ-ባህርያቱን በሚስልበት ወቅት ተአማኒነታቸውን ዘላቂነታቸውን.. የራሱን ያህል በሚያውቃቸው ደረጃ ላይ ለመሆኑ በጥብቅ ሊገነዝብ ይገባል፡፡ ታሪኩ ሲጀምር የምናገኘውን የገፀ-ባህሪ እምነትና አስተሳሰብ በየምዕራፉ ያለአሳማኝና በቂ ምክንያት እየተለዋወጠና እየተቀያየረ ካገኘነው የማንን ምንነት ሳንረዳ እንደገበቴ ውሀ መዋለል ነው ትርፉ የሚሆነው፡፡

ስለዚህም <u>በከርታታው</u> ልቦለድ መጽሐፍ ውስጥም ተስሎ የምናገኘው ዋና ገፀ-ባህሪ አያልቅበት አለሙም ከታሪኩ ጥንስስ ጀምሮ እስከ ፍፃሜው ድረስ የምናገኘው ሲሆን፤ ይሁንና ግን ደራሲው በርዕቱም ሆነ በኢ-ርቱዕ የገፀ-ባህሪ አቀራረብ መንገድ የአያልቅበትን ህሊናዊ ባህሪ ከአካላዊ መልኩ እጅግ ተቃራኒ በሆነ መንገድ -በበዛ መለኩ /እጅግ በበዛ መልኩ/ አቅርቦልን እናገኛለን፡፡

በመጽሐፉ ውስጥ ደራሲው የአያልቅበትን ህሊናዊ ባህሪ ከአካላዊ መልኩ በተሻለ ማቅረቡ ምን ያህል ህሊናዊ ባህሪው ላይ አፅንኦት ሰጥቶ ሊያሳይ የፈለገው ጉዳይ እንዳለ እንረዳለን፡፡ በመጀመሪያ የአያልቅበትን ውስጣዊ ባህሪ ለመቃኘት ስንሞክር ከታሪኩ የምንረዳው አያልቅበት ትሁት፣ደግ፣ሰውወዳጅ… የመደረጉ ሰበብ የሚያውቁት ሰዎች እንደሚሉት "…አያልቅበት እንደ ስሙ ትህትናው ፣ ደግነቱ፣ቁመነገሩ፣ፍቅሩ የማይነጥፍ ሰው ነው፡፡" /ከርታታው ፥ ገፅ ፥ 248/ ለወዳጁና ለአብሮ አደግ ጓደኛው ለከርታታው የሙት መንፈስ አደራ ሲል ነው፡፡

አያልቅበት የልቦለዱን ታሪክ እያዋዛ የሚተርክልን ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ መፅሀፎቹ ለህትመት የበቁለት ደራሲና ጋዜጠኛም ጭምር መሆኑን በሶስተኛ ወገን ተነግሮናል፡፡ እኔ የጥሩ ባህሪ ባለቤት ነኝ፣ ፀሀፊና ጋዜጠኛ ነኝ ብሎ የሚኮፈስና የሚኮራ ሰውም አይደለም፤ ስለራሱ ራሱ ከመናገሩ ይልቅ ሌሎች ሲመስክሩ ከመፅሀፉ እንዲህ እንረዳለን " አባባ!ጋሼ አያልቅበትን በመልክ ባላውቀውም በፃፋቸው መጽሐፎቹ አውቀዋለሁ፡፡ መጽሐፎቹን ደጋግሜ አንብቤ አቸዋለሁ…"/ከርታታው ፥ ገፅ ፥149/ ብላ ዘነበች የተባለችው የአብዬ ሀምዛ የልጅ ልጅ ስለደራሲነቱ የምታውቀውን ትመሰክራለች፡፡ በሌላ ገፅ ደግሞ ሌላው የአብዬ ሃምዛ ልጅ የሆነው መምህር ፈለቀ የአያልቅበትን ማንነት ለወዳጅ ዘመዶች እንዲህ አርጐ ሲያስተዋውቅ በመጽሐፉ በግልፁ ይነበባል፡፡" …የመጀመሪያው በመምህርነት ሙያ የሚያገለግል ሲሆን ሁለተኛው ደግሞ የታወቀ ጋዜጠኛ ነው፡፡" /ከርታታው ፥ ገፅ ፥ 278/ ብሎ ጋዜጠኝነቱን ይመሰክራል፡፡

አያልቅበትን በህሊናዊ ባህሪው ስንመለከተው ቁመነገረኛና ለአብሮ አደግ ጓደኛው ሙት መሆኑንና ቃሉንም ለመፈፀም ወደኃላ የማይል መሆኑን ባለፈው ገፅ አይተናል፡፡ ይህ ቁምነገረኛነትና ደግነት በገሀዱ ዓለም እንደምናውቀው አንድ ሰው ባህሪውን ከቤተሰቡ፣ ከአስተደደጉ ፣ ከወጣበት ማህበረሰብ እምነትና ባህል እንደሚወርስ ሁሉ ፦ በዚህ መፅሀፍ ውስጥ የምናገኘው አያልቅበትም ህሊናዊ ባህሪውን ከወላጆቹ በተለይም ከወላጅ አባቱ እንደወረሰው ይገለፃል፡፡

ከታሪኩ እንደምንረዳው የአያልቅበትን ሕሊናዊ ባህሪ የሚያጉሉ ገለፃዎች ሰፋ ባለ ሁኔታ ቀርበዋል፡፡ ይህንን እሳቤ ይዘን ታሪኩን በጥልቀት ስንቃኝ የምንረደውና የምንመለከተው አያልቅበት የተከበረና ተወዳጅ ሰው ፣ሩህሩህና ደግ… መሆኑን ከአባቱ እንደወረሰው እንደሚከተለው ተገለፆልን ይገኛል፡፡

> "…አባትህ አለሙ ሩህሩህና ቸር ነበር፡፡ ስሙን በሚያውቀው ሁሉ ከፍተኛ ከበሬታን ያተረፈ* ለተቸገረ እጁን የማያጥፍና ረጂ ነበር፡፡ ሀቅን የሙጥኝ ብሎ እስከ መጨረሻው የኖረ የአገር አድባር በመሆን የተጣላውን አስታራቂና የሸሸውን አቅራቢ ስለነበር በትነሹም በትልቁም ዘንድ ትልቅ ሞገስ ያገኘ ሰው ነበር፡፡… አለሙ ለአካባቢው ሕዝብና ለእኛም ጭምር ታማኝነትን ፣ሀቅን፣ ርህራሄንና ደግነትን አስተምሮ አልፏል፡፡" /ከርታታው ፥ ገፀ ፥ 127/ብለው አብዬ ሀምዛ ቁልጭ ባለ መልኩ የአያልቅበት አባትን ባህሪ ገልፀዋል፡፡

ከዚህ ከአብዬ ሀምዛ የአያልቅበት አባት የባህሪ ገለፃ እንደተረዳነው አያለቅበት ደግነቱን፣የዋህነቱንና፡ ቁምነገረኛነቱን ከአባቱ እንደወረሰ ነው፡፡ ይህ ቁም ነገረኛነቱ፣ የዋህነቱና ደግነቱ ደግሞ የፈጠሩበት ነገሮች ቃልኪዳኑን እንዲጠብቅ አብቅተውታል፡፡

አያልቅበት ለራሱ ጥሩ ስም፣ በጐ ሥራ ሲልና በማህበረሰቡ ዘንድ ያተረፈውን የጥሩ ሥም ባለቤትነት ሰንደቁን አጉልቶ ለማሳየት ወደ ትውልድ ቦታው ከጓደኛው ጋር ተጓዘ፡፡ የከርታታውን የሙት አደራ በሚገባ ለመወጣትም ወሰነ፡፡ እነዚህ ተፅዕኖዎች የፈጠሩበት ባህሪያቶቹ ለወዳጁ ለከርታታው ቃሉን በመጠበቅ አደራውን ከግብ ለማድረስ እንዲነሳሳ ሆኗል፡፡ ለከርታታው ሙት መንፈስም ቃሉን እንደሚጠብቅ በሚከተለው መንገድ ተገለፆ እናገኛለን፡፡ "… ቅሬታዬን አምቄ በመያዝ የጠየቀኝን ለመፈፀም ፈቃደኛ መሆኔን በአወንታ ራሴን ወደ ፊትና ወደ ኃላ በመቀለስ ምልክት ሰጠሁት፡፡"/ ከርታታው ፥ 40/

አያልቅበት የተማረ ከመሆኑም በላይ ከዕድሜውና ከኑሮው እንዲሁም ከማህበራዊ ህይወቱ ብዙ ዕውቀት የቀሰመ ሰው የመሆኑን ያህል፤በድርሰቱ ላይ የተሳለው ህሊናዊ ባህሪው አንዳንድ ጊዜ የተለያየ ማንነት ያለው ገፀ-ባህሪ ሲያስመስለው ይታያል፡፡ ይህም የገፀ-ባህሪውን በድርሰቱ ውስጥ ወጥ ሆኖ አለመቅረብ/አለመሳል/ ቁለጭ አርጐ

ያመለክታል፡፡ ገፀ-ባህርያት ከሚኖራቸው የራስ የሆነ አመለካከት፣ የራስ የሆነ አስተሳሰብና ፍልስፍና አንፃር ሁልጊዜ ወጥ እንዲሆኑ ይፈለጋል፡፡

አያልቅበት አለሙም ቃል አክባሪነቱን፣ሰው ወደጅነቱን፣ቁመነገረኛነቱን፣ደግነቱን እንዲሁም የአርቆ አስተዋይነቱን ያህል እምነቱንና አመለካከቱን በተመለከተ ግን ንፋስ እንደመታው ዛፍ አንዴ ወደቀኝ አንዴ ወደግራ ሲል ይስተዋላል፡፡“ ጉድ ፈላ አኮ እባካችሁ! ይህ የቀየው ጂኒ፣ሰይጣን፣ቅብርጥሴ የሚሉት ነገር ይሆን እንዴ? …“/ ከርታታው ፥ 31/

ብሎ ይለንና በዛው ገፅ ላይ ደግሞ ከዚህ ገለፃ በተቃራኒው መንገድ የተምታታና ግራ በሚያገባ መንገድ አስተሳሰቡን ያሳየናል፡፡“ … ሰይጣንን የፈጠረው የሰው አእምሮ ስለሆነ እኔ በበኩሌ አለ ብዬ ከቶ አላምንም…“/ከርታታው ፥ 31/ ይልና በሚቀጥለው ገፅ ሌላ እርስ በእርሱ የተሳከረ ዕምነትና አመለካከት ሲኖረው በግልፅ እንመለከታለን፡፡ “ … እኔ በበኩሌ እስከማውቀውና እስከምረዳው ድረስ ሰይጣን ጥበብ አፍቃሪ፣አዋቂ፣ብልህ ማለትነው፡፡ይህ ደግሞ በብዙ ልሂቆች ተመስክሯል…“/ከርታታው ፥32/ብሎ አንዱ ከአንዱ እጅግ የተመታታና የተቃረነ /የተጣረሰ/ ዕምነትና አመለካከት ይነግረናል፡፡

በሌላ በኩል ደግም ይህ አይነት ህሊናዊ ባህሪ፣ወጣ ያለ ግላዊ ዕምነትና አመለካከት ያለው /ከማህበረሰቡ በተለየና በራቀ መንፈስ/ ለማለት በሚቻል መልኩ አያልቅበት እንደገና ወደ ማህበረሰቡ እሳቤና አመለካከት ውስጥ ተመልሶ ይዘፈቃል፡፡ የጓደኛው፣የከርታታው የሙት መንፈስ እንዳይወቅሰው የግል ዕመነቱንና አስተሳሰቡን በገሀድ ሲጥስ ይታያል፡፡ ቃሉን ሊፈፅም ምን ያህል ርቀት ሊጓዝ የሚችልበት አስተሳሰብና ዕምነት ከየት አመጣ? የሚለው ጥያቄ የተደራስያኑ ጥያቄ ሊሆን እስከሚችል ድረስ ደራሲው ግን ገፀ-ባህሪውን ባለ እንደዚህ አይነት ህሊናዊ ባህሪ ባለቤት አርጐ ሊያቀርበው ችሏል፡፡

በድርሰቱ ውስጥ ዋና ገፀ-ባህሪ ሆኖ ያወቅነው ይህ ገፀ-ባህሪ ህሊናዊ ባህሪው ከአካላዊ መልኩ ሰፋ ባለ ሁኔታ በመቅረቡ ደራሲው ትኩረት ሰጥቶ ሊያሳይ የፈለገው ይህንን ጉዳይ ይሆን ብለን ከዚህ በፊት ባለው አንቀጽ አይተናል-ተረድተናል፡፡ በሙያው መምህር ፣ ጋዜጠኛና ደራሲ ነው የተባለው ይሄ ገፀ-ባህሪ ወደዚህ ሙያ እንዴት እንደገባ አንባቢ በቅጡ አይረዳም ከራሱ ከገፀ-ባህሪውም ምንም የተባለ ነገር የለም፤በገለፃም ስለደራሲነቱ የሚታወቅ የለም፡፡ ደራሲው የአያልቅበትን መኖሪያ ቤት በገለፃ ባለማስቃኘቱ ገፀ-ባህሪው ደራሲ ለመሆኑ አንባቢ እንዳይረዳ አርጓል፡፡ የቤቱን ስዕላዊ ገለፃ አንባቢ በምንም መንገድ አይረዳም ስለሚስቱ ብቻ በጥቂቱ ነግሮን ያልፋል እንጂ…“ባለቤቴ ስለከርታታው ህመም ተጨንቃ ስለነበር ጋሼ ከርታታው እንዴት ነው?ዶክተሩስ ምን አለው? ብላ ስለጠየቀችኝ ሀኪሙ ያለውን ነገርኳት” /ከርታታው፥12/ የቤቱን ሁኔታ

የመጽሐፍት መደርደሪያውን በማሳየት ፣የፅህፈት ጠረጴዛውን በማስቃኘት ስለ ደራሲነቱ ለአንባቢ የሚሰጠው ስዕላዊ መግለጫ የለም፡፡

ሌላው የሚገርመው ጉዳይ እንደዋና ገፀ-ባህሪነቱ በሌሎች ተመሳሳይና ተዛማጅ በሆኑ  የጥበብ ስራዎች ፍቅር ውስጥ መሆን አለመሆኑንም አንባቢ አይረዳም ግጥም ይወደል… ዘፈንስ? አይታወቅም፡፡ እንግዲህ ይህ ገፀ-ባህሪ ነው ጋዜጠኛና ደራሲ ተብሎ በደፈናው የተነገረው…? ይህ ደግሞ ከባህሪው ደግነቱንና ቁመነገረኝነቱን አጉልቶ ደራሲነቱንና ጋዜጠኛነቱን አኩስሶ የሙሉ ስብዕና ባለቤት ነው ቢባል አያዋጣም፡፡ ደራሲ የተባለው ቅፅል ስምም አይገባውም ያስብላል፡፡

### 3.2.2. የከርታታው አልዩ ሙት መንፈስ

ለዚህ ልቦለድ ድርሰት መፃፍ መሠረቱ /ለታሪኩ ፍሰት ወደፊት መግፋት/ ምክንያቱና ወሳኙ የልቦወለድ ታሪኩ መነሻ ዋና አስኳል የሆነው ከርታታው ነው፡፡ ከርታታው አልዩ የልቦለዱ ጥቂት ገፆች ላይ ብቻ በልቦለዱ ውስጥ በህይወት  የምናገኘው ፤በኂላም ነፍሱ ከስጋው ከተለየች በኂላ የሙት መንፈሱ እየተመላለሰ ለአብሮ አደግ ጓደኛው ለአያልቅበት የሚከሰትና እስከ ታሪኩ ፍፃሜ ድረስ የምናገኘው የታሪኩ ትልቅ ምዕራፍና አንኳር ሁኖ የሚገኝ ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ ይህ ገፀ-ባህሪ ለምን ለጥቂት ጊዜያት ብቻ ኖረ ? ለምንስ እስከ ታሪኩ ፍፃሜ /ከሞተ በኂላ በመንፈስ/ እየተገለፀ ታሪኩን ሊተርክ ተደረገ? ቢባል- መልሱ ከአፃፃፍ ከቴክኒክ አኳያ የሚመለስ ይሆናል፡፡ ደራሲ በጽሐፉ ውስጥ ያሉትን ገፀ-ባህርያት የማስታመም የማዳን፣ደግም ሆነ ክፉ/እኩይ/ ባህሪ የመስጠት፣ ቆንጆም ሆነ ፉንጋ የማድረግ ሙሉ መብትና ስልጣን አለው፡፡ ስለዚህ የዚህ መጽሐፍ ደራሲ ከርታታውን ገሎ በሙት መንፈስ ነፃ ሆኖ እንዲተርክ ማድረጉ ብዙ ምክንያቶች አሉት፡፡

የመጀመሪያው ምክንያት ከርታታው ባይሞት ኖሮ በአንደኛ መደብ የተጀመረውን የትረካ አንፃር ሌላ ተራኪ ስለሚኖርበት ሁለት ተራኪዎች በመጽሐፉ መምጣት መፅሀፉን ያጨናንቁት ነበር፡፡ ከርታታው በራሱ መንገድ መተረክ እና አያልቅበት በሌላ መንገድ መተረክ የተመታታ የትረካ አንፃር ይመጣል ከሚል ግምት፤

ሁለተኛ ከርታታው እንደሚሞት በአያልቅበት በኩል ከመሞቱ አስቀድሞ የተለያዩ ንግሮች በመፅሀፉ በመገኘታቸው ከርታታው ከሞት በኂላ እንዲተርክ ምክንያት ሆኗል፡፡ አያልቅበት የተባለው የከርታታው ወዳጅ የጓደኛውን መሞት በንግር የገለፀባቸው ቦታዎች….

> "… አንድ ነገር ጅስሜን እንደ ውሪት አየተሰማውና
> አየነዘረው፡፡" /ከርርታታውን ፥ 7/

ይህ ዐ.ነገር የከርታታውን መሞት በንግር የሚገልፅ ነው፡፡ ሌሎችም ዐ.ነገሮች ያን ያመለክታሉ፡፡

> " … ከወትሮው የበለጠ ውስጤ በፍርሀት እየታረሰ
> ብቻ ሳይሆን እየተቀረደደም…" / ከርታታው፥10/

እነዚህ ሁሉ በመጽሐፉ ውስጥ የሚገኙ ገለፃዎች የከርታታውን መሞት የሚያመለክቱ ንግሮች ናቸው፡፡

በሶስተኛ ደረጃ ከርታታው በመንፈስ ሆኖ የመተረክ ምክንያቱ ያደገበት ማህበረሰብ ወግና ባህል ነው፡፡ ከርታታው ያደገበት ማህበረሰብ በጣም ወግ አጥባቂና ያለጋብቻ የሚፈፀምን ወሲባዊ ግንኙነት የሚኮንን በመሆኑ የከርታታው ከሕመሙ መትረፈና የልጁን፣የልጁን እናትና ወላጅ እናቱን ራሱ ሄዶ ከመፈለግ አንጻር ሲታይ በህይወት እያለ ከሚያረገው ይልቅ ሞቶ በመንፈስ የሚያደርገው ትረካ ነፃነቱን ስለማይጋፋ / ጠያቂም ወቃሽም/ የሌለው እንደልቡ ሆኖ እንዲተርክ ሲባል ሞተ፡፡ ይህም ከህሊና እዳ መላቀቅ የመጣ ነው፡፡

> " …በአገራችን የተለመደው ከንፈር መሳምና ልጅቱ ስታገባ ልዩ ልዩ ስጦታ መስጠት ነው፡፡… ልጅቱ በምታገባበት ጊዜ ከነድንግልናዋ ካለተገኘች ግን አግቢው በቀጋ እየሟዥቀና በአለንጋ እየገረፈ ህግዋን የገሰሳትን ሰው እንድትናገር ያስገድዳታል፡፡ ይህም እስከ ግድያ ስለሚያደርስ ከንፈር ወደጆች ፍቅራቸውን የሚጨርሱት በመሳሳም ብቻ ነበር፡፡ … በዚህ ላይ ቤተሰቦቿ ከሰሙ ድምጥማጤን ጨርሰው ያጠፉታል፡፡ ስለዚህ የነበረኝ ምርጫ ፀሀይን ለመከራ አጋፍጬመኮብለል ብቻ ስለነበር ትቻት ደሴ ገባሁ…" /ከርታታው 210/

በነዚህ ምክንያቶች የተነሳ ከርታታው በመንፈስ ተገልፆ እንዲተርክ ተደረገ፡፡ አንዱ የተራኪዎች መደራረብ መጽሐፉን ያለመጠን እንዳይለጥጡትና የተመታታ የአተራረክ ስልት /ቴክኒክ/ እንዳይመጣ፤ ሌላው የከርታታውን ሞቶ የመተረክ ነፃነት ከመፈለግ አንፃር ነው፡፡ ከርታታው ወደፊት ሚስቱ ልትሆን የምትችለውን ጥሩ የከንፈር ወዳጁን /ፀሀይን/ ጥንቃቄ በጐደለውና የአካባቢውን ባህል በጣሰ መልኩ የግብረስጋ ግንኙነት ማረጉ ሕሊናን የሚነካ ጉዳዩ ስለሆነና ባህሉም ስለማይፈቅድ ያለምንም ረዳት በረሃ ላይ ጥሏት በመጥፋቱ ምን ያህል በአከባቢው ሰው ልትወገዝ እንደምትችልና ዝሙተኛ ተብላ አድሜዋን ሙሉ እንደምትገለል ስለተገነዘበ በታሪኩ በጸጸት ጠጥቶ እንዲሞት ሆነ፡፡

ሌላው ከርታታው ሞቶ እንዲተርክ የተደረገበት ምክንያት የድርሰቱን ጭብጥ አጉልቶ ከማሳየት አንጻር ከሚል የመነጨ ነው፡፡ የሙት መንፈስን ምንነት ለአንባቢው ለማስገንዘብና ለማሳየት እንደማለት ነው፡፡

> "ቅድም ጀምራችሁ ሙት መንፈስ እያላችሁ የምትናገሩት ግራ ሆነብኝ። ይህ በየቀየው አመድለአመድ የሚልከሰከሰው ዛር ውላጅ ፥ ጂኒ ማለታችሁነው? "/ከርታታው፥ 208/

የሚለውን የሙት መንፈስ ያልገባቸው የገፀ-ባህርያት ጥያቄ ስለሙት መንፈስ ምንነት ለአንባቢው ለማሳወቅና የመጽሐፉን ጭብጥ አጉልቶ ለማሳየት ነው። በዚህም ምክንያት ከርታታው በሙት መንፈስ ሆኖ እንዲተርክ ተደረገ። "ጂኒ ወይም አጋንንት ሳይሆን የሞተውን ሰው መስሎ የሚከሰት ነገር ነው…" /ከርታታው ፥ 208/

> "ሰዎች ከሞቱ በኂላ ለሚወዷቸውና ለሚቀርቧቸው ሰዎች ሙትመንፈሳቸው እየመጣ እንደሚያነጋግራቸው ማንበቤ ትዝ ይለኛል። ስለዚህ ለአያልቅበት የተከሰተው የከርታታው ሙት መንፈስ ወይም ጉስት እውነት የማይሆንበት ምክንያት የለም።" /ከርታታው ፥ 208/

በእነዚህ ከላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች የተነሳ የከርታታው የሙት መንፈስ በሙት መንፈስ ሆኖ መተረክ በመጽሐፉ  የተለየ የአፃፃፍ ቴክኒክ ለማሳየት የመጣ ምክንያት ነው።

በልቦለዱ ውስጥ ደራሲው ከርታታውን በእንዴት አይነት አካላዊ መልክና ህሊናዊ ባህሪ ገለፀ ወደሚለው እና ወደ ትንተናው ዋነኛ አካል ስመጣ ይህን አገኛለሁ።

### 3.2.2.1 የከርታታው አልዩ አካላዊ መልክ

በታሪኩ ውስጥ አርባ ሶስት ዓመቱ እንደሆነ የተገለፀለት የልቦለዱ የጀርባ አጥንት የሆነው ከርታታው አካላዊ መልኩ  ፈገግታ ከፊቱ የማይጠፋ - ባለ ቀጭን አንገት ባለቤት እንደሆነ የታሪኩ መጀመሪያ አካባቢ ደራሲው በአያልቅበት አንደበት ከገለፀልን በኂላ ከርታታው ይሞታል። ከሞተ በኂላ የሙት መንፈሱ ለአያልቅበት በሚገለፅበት ጊዜ /በገሀድ ያለ እስኪመስለው ድርስ/ ለአያልቅበት በተከሰተበት ወቅት የከርታታው አልዩ አካላዊ መልክ እንዲህ ተገልጿል ።

> " .ቁመቱ፣ዛላው፣የራሱ ሾጣጣነት ፣ የግንባሩ ስፋት፣የአፈንጫው ርዝመት፣ አገጩ… መቃ የመሰለ ቀጭን አንገቱ በጠቅላላው ሁለንተናው እንዳለ ቁርጥ ከርታታውን ነው፡… በረዶ የመሰለ ፍንጭት ጥርሱ ፈገግ ሲል…" /ከርታታው ፥ 32/

በዚህ አካላዊ መልክ ገለፃ ላይ ርቱዕ በሆነ መንገድ ማለትም ተውኔታዊ ባልሆነ /ኢ-ርቱዕ/ መንገድ ከርታታውን ሲገልፀው … "ቁመቱ… ዛላው" የሚሉት ገለፃዎች የከርታታውን በቁመት መርዘም በተዘዋዋሪ መንገድ የሚገልጹ  ሆነው ከመገኘታቸውም ባሻገር "…ከሳና በጨጭ ከማለቱ በስተቀር ቁርጥ ያው ራሱ ከርታታውን ነው።" /ከርታታው፥32/ የሚለው አያልቅበት ከርታታውን የገለፀበት አካላዊ መልክ ገለፃ የከርታታውን አካላዊ መልክ

አንባቢው እንዲያውቅና በመጠኑም ቢሆን በምናቡ ምስል ስሎ የልቦለድ ታሪኩን እያነበበ የከርታታውን ቅርፀ ሰውነት አእምሮው ውስጥ ከትቦ እንዲያስቀምጥ ደራሲው መጠነኛ ሊባል የሚችል ሙከራ አድርጓል። ምንም እንኳን የገፀ-ባህሪውን የተሟላ ምስል ባናገኝም የተገለፀው አካላዊ መልኩ አጠቃላይ ስብዕናውን ከማጉላት አንፃር ስናየው የተሻለ ሆኖ ተገኝቷል። ለምን ቢሉ ከላይ የተጠቀሱት '... ከሳና ፣ በጨጭ' የሚሉት የመልክ ገለፃዎች ወደፊት ከምናየው የገፀ-ባህሪው ስብዕና በተለይ የቁጭት ባህሪውን /ስብዕናውን/ ከማጉላት አንፃር ከፍ ያለ አስተዋፅኦ አበርክቷል።

ሌላውና ዋናው ከከርታታው አካላዊ መልክ ጋር የሚያያይዘው አለባበሱ ነው። በምንም አይነት መንገድ የአለባበሱ ሁኔታ ለተደራሲ አልተገለፀም /ይህ የአለባበስ ገለፃ በዚህ ገፀ-ባህሪ ብቻ ሳይሆን በሌሎችም ላይ የሚታይ ነው/ ስለዚህ የአለባበሱ ጉዳይ ባለመገለፁ ስብዕናውን ለማወቅ ለሚደረገው የአንባቢ ጥረት ትልቅ እንቅፋት ፈጥሯል። ምክንያቱም ቁጭት እና ፀፀት ያለበት ሰው አለባበስ ምን አይነት እንደሆነ ተደራሲው ይረዳልና ነው።

የደራሲው ገፀ-ባህርያት አሳሳል ላይ በተለይ አካላዊ መልክ በበቂ ሁኔታ ተስሏል አልተሳለም በሌሎች ገፀ-ባህሪያት ላይ ወደፊት የምናየው ጉዳይ ቢሆንም ወደ ከርታታው ህሊናዊ ባህሪ ገለፃ እንሂድ፡-

### 3.2.2.2 የከርታታው አልዩ ህሊናዊ ባህሪ

አንድ ገፀ-ባህሪ የተቀረፀበትን ባህሪ ቋሚ በሆነ መልኩ በልቦለድ ውስጥ ሲተገብረው እንጂ የሚናገረውን ወይም በሁለተኛ ወገን ገፀ-ባህሪው እንዲህ አይነት ነው ተብሎ የሚነገርለትን ህሊናዊ ባህሪ ሳይሆን ሲቀርና የኑሮ ትግበራው ከተወራለትና ካወራው የተለየ ሲሆን ተደራሲው " ፍየል ወዲያ ቅዝምዝም ወዲህን" ሊተርት ግድ ይላል።

በልቦለዱ ውስጥ በተደጋጋሚ ጊዜ ሲገለፅ እንደተሞከረውና እንደተገለፀው የከርታታው ህሊናዊ ባህሪ እዚህ ቀረህ የማይባል ሁኖ ፤ በተማረና በሰለጠነ ማህበረሰብ እሳቤ ተኮትኩቶና ተገንብቶ እንዳደገ ሁሉ የተሞረደና የነጠረ ስብዕና ባለቤት ያለው ነው። ከልጅነቱ እስከ እውቀቱ ከዛም እድገትን ፣ ስልጣኔንና መልካምነትን በሳቅና በፈፈገግታ አጅቦ እያስተማረ ለወገኑ እንዲሁም ለፍቅሩ ራሱን አሳልፎ የሰጠም ተደርጐ ተስሏል። ይሁንና ግን ከዚህ በመቀጠል የሚታዩት አንዳንድ የከርታታው የተለያዩ የውስጥ ማንነት መገለጫዎች እሱነቱን ይገልፃሉ ወይ ተብሎ ቢጠየቅ የገፀ-ባሪው አንዳንድ ባህርያቶቹ /በጉም ይሁን መጥፎ ፡ ለነገሩ ደራሲው ብዙም የተጋነነ መጥፎ ባህሪ ባይሰጠውም/ ምንጫቸው ምን እንደሆነ የሚከተለው ትንተና ይነግረናል።

የከርታታው እያንዳንዱ ሕሊናዊ ባህሪ አንባቢ በሚገባ እንዲገነዘበው ተደርጐ ቀርቧል። በትክክልም አልፎ አልፎ ከምናገኛቸው ገለፃዎች በመነሳት የምንረዳው ጥቂት

ነገር አለ፡፡ በመጽሐፉ በቅድሚያ የምናገኘው የገፀ-ባህሪውን ትህትና፣ታዛዥነትና ጨዋነትን ነው፡፡ "… ከርታታው በሄደበት ሁሉ ጥርስ የማያስከድን ተጨዋች ቡቡና ትሁት፣ለሁሉ ታዛዥና አንደበተ ርቱዕ …" /ከርታታው ፥ 16/ ተብሎ ይገለፅልናል፡፡

ሌላው ከርታታው ሲበዛ ቀልደኛና ፌዘኛ መሆኑን ነው፡፡ የሚያፌዘው ፣ የሚቀልደውና የሚፈላሰፈው በራሱ ላይ ብቻ አይደለም፡፡ ከዚያም ያልፋል፡፡ በመጠጣትህ ምክንያት ለዚህ አይነት የከፋ ስቃይ ተዳርገሀል፣ተስፋም የለህ ብለው ለሚሉት ጓደኞቹ እንኳን በራሱ ላይ እየቀለደ ይናገር ነበር፡፡ በሞቱ መምጫ ሰዓት /ልክ በአስራ አንደኛው ሰዓት ጭምር/ አበቃለት ተብሎ የከፋ ደረጃ ደርሶ እንኳን ስለመጠጣቱ እንዲህ ብሎ ያፌዛል"… በሰማይም ለዚህ ያበቃኝ መጠጥ ይኖር የሆን? እያለ ያስቀን ነበር "/ከርታታው፥17/ ይህ ንግግሩ አንግዲህ የሱን ቀልደኝነትና ፌዘኝነት ይበልጥ ያጉላል፡፡ ስለከርታታው ህሊናዊ ባህሪ ከታሪኩ እንደምንረዳው አእመሮው በትምህርት ቢበለፅግም ፣ ቅንና ሩህሩህ ቢሆንም ስብዕናው በመጠጣቱ ምክንያት ዘቅጧልና ይህ ዝቅጠት በዙሪያው በተፈጠሩና ከቁጥጥሩ ውጪ በሆኑ ድርጊቶቹ የመጣበት መሆኑን ለማጉላት ጠንከር ያለ ገለፃ /ንግግር/ እንዲያደርግ ተደርጐ በደራሲው መሳሉን ያመለክታል፡፡

በመጠጥ ምክንያት ለዚህ በቃሁ ብሎ መጠጥን ከመኮነን ይልቅ ለጠጪነት የዳረጉትን ነገሮች ቁጭቱንና ፀፀቱን ቀድሞ ማጥፋት ይገባው ነበር፡፡ "… ቀድሞውኑ ያንተን ምክር ብቀበል ኖሮ መቼ ለዚህ እደርስ ነበር ብለህ ነው፡፡ እንግዲህ የመጣውን ከመቻል በስተቀር ምን ይደረጋል፡፡ የኔ ነገር ሆዱን ያለ ሆዱን ተወጋ አንደተባለው ነው፡፡ ንድማና የፈሰሰ ውሃ ወደ ኋላ ተሂዶ አይዘገንም፡፡ " /ከርታታው ፥ 13/ ብሎ ለጓደኛው ለአያልቅበት ፀፀትና ቁጭት ባዘለ ድምፀት ይነግረዋል፡፡

በመቀጠል የምናየው የከርታታው ውስጣዊ ባህሪ መገለጫዎች ችኩልነቱ ነው፡፡ በድርሰቱ የችኩልነትን መዘዝ ለማጉላት በሚደረግ ጥረት መሀል የከርታታውን ውስጣዊ ባህሪ ይገልፃል፡፡ ከርታታው በችኩልነቱ የተነሳ ከከንፈር ወዳጁ ጋር በፈፀመው ስህተት ምክንያት ልጅቱን ለአጉልና ለከፋ የባህል ወጥመድ አጋልጧት ጠፋ፡፡ እሱንም ከሆድ ለማይወጣ ትልቅ ፀፀትና ቁጭት ዳረገ፡፡ ይህም የችኩልነት ጣጣ ክሩን እየመዘዘ ሄዶ እሱን ለሞት እሷን ጠባሳው ለማይሽር የልጅነት የሰቀቀን ፍቅር አብቅቷታል፡፡

ከርታታው በሁለት የውስጣዊ ባህርያት የተወጠረ ገፀ-ባህሪም ሆኖ ተስሏል፡፡ በአንድ በኩል ሩህሩህነትና አገርን በቅን የማገልገል ፍላጐቱ በሌላ በኩል የውስጥ ቁጭቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ሁለት ባህሪያትም ወደተለያዩ አቅጣጫዎች ይጐቱታል /ይስቡታል/ ልክ እንደ ሱስ፤አካባቢውን ለማልማት ፣አገርን ለመጥቀም በአንድ ወገን በሌላ ወገን ደግሞ በቁጭት ምክንያት ይዋትታል፡፡ "… ቅዳሜና እሁድ ከተማሪዎች ጋር ሆኖ መንገድ ያፀዳል ፣ የውሃ መሄጃ ቦይ ይቀዳል፡፡ የድሆችን ቤቶች ይጠግናል፡፡ በየምክንያቱ ወደ ትመህርት ቤት መግባት ያልቻሉ ልጆችን ማታማታ በነፃ ያስተምራል፡…፡፡"/ከርታታው፥85/ ብለው

አብረውት በአስተማሪነት ይሰሩ የነበሩት አቶ ይማም ይገልፃሉ፡፡ የውስጥ ቁጭቱን ደግሞ እንዲህ በማለት ለአያልቅበት ይገልፃል "… ቀድሞውኑ ያንተን ምክር ብቀበል ኖሮ መች ለዚህ እደርስ ነበር ብለህ ነው፡፡"/ከርታታው ፥ 13/ ይላል፡፡ በነዚህ ሁለት መንታ ሃሳቦች /ባህርያት/ ተወጥሮ በመያዙ ምክንያት አእምሮው ተጨናንቆ በጣም ይጠጣል፡፡ በመጨረሻም ወደ አንዱ አድልቶ ወይ ሩህሩህነቱንና ለአገር አሳቢነቱን ይዞ መቀጠል ሲያስብ በሌላ በኩል ቁጭትና ፀፀት ውስጡን ይበላው ስለነበር በጣም ይጠጣል፤በዚህም ለሞት ሲዳረግ በድርሰቱ ይታያል፡፡ እንግዲህ የከርታታው ህሊናዊ ባህሪ ይህን ይመስላል፡፡ ከረጅም ልቦለድ የገፀ-ባህርያት አቀራረፅ መርህ አንዱ የሆነውን ኢ-ፍፁምነትን የተላበሰ ነው፡፡በመሆኑም የከርታታውን ሕሊናዊ ባህሪ ለመሳል ደራሲው የተጠቀመበት መንግድ ከዘመኑ አፃፃፍ ጋር ሲታይ የማይተናነስ ሆኖ በመገኘቱ አንባቢን የህሊናዊ ባህሪው ተመልካች በማድረጉ የተዋጣለት ስራ ነው፡፡

ይህ የከርታታው ህሊናዊ ባህሪ በተደጋጋሚ ጊዜ ስለተገለፀ በጠቅላላው የከርታታውን ባህሪ በአጭር መንገድ ትጉህና ለዕድገት ስለቸኘን የማያውቅ አውቆ አወቅ የሚል መልካም ባህሪ ባለቤት ነው ልንል እንደፍራለን፡፡ ደራሲው በገፀ-ባህሪው የውስጥ ባህሪ ላይ የተሳሳተው ወይም ሳይገነዘብ የቀረው ነገር ግን የከርታታው አልዩ ህሊናዊ ባህሪ አሳሳል ገፀ-ባህሪው እንዲያስተላልፍ ከተሳለበት አላማ አንፃር ስናየው እጅግ ትለቅ የሆነ ልዩነት ወይም ክፍተት ማሳየቱ ነው፡፡

በልቦለዱ ውስጥ በህሊናዊ ባህሪው ሩህሩህ ፣አስተዋይ ፣ትሁት አገር ወዳድና አፍቃሪ የመሆኑን ጉዳይ ደራሲው ደጋግሞ ከመግለፁ በስተጀርባ…የተሳለበት አላማ ከሱ የኑሮ አካሄድ ጋር አለመጣጣሙን ስንገነዘብ ጥያቄ ያጭርብናል፡፡

በእርግጥ በመጽሐፉ የተሳሉት የተለያዩና ብዛት ያላቸው ገፀ-ባህርያት አንደገለፁልን ከርታታው አልዩ ደግ፣ለህዝብ ሟች፣ለፍቅር የሚሰዋ-አላማውን እስርም ሆነ ሞት ሊበግሩት ያልቻለ ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ ግን ግን ይህን ያህል በመልካም ህሊናዊ ባህሪ የተገነባ የታነፀና የተሳለ ሠው-በእርግጥ ይህን የሌሎች ገፀ-ባህርያት የቃላት ሙገሳና አድናቆት-ከርታታው አልዩ ኑሮታል ወይ? ወይስ በገሀዱ አለም እንደሚከሰተው-ሰው ከሞት በኂላ ወቀሳን በመፍራት በጐነቱን ብቻ እንጂ ድክመቱን የመግለፅ መጥፎ የባህል ወረርሽኝ /ችግር/ በመጽሐፍም ላይ አለ ወይ? የሚያስብል ነው፡፡ የሚከተሉትን እንደምሳሌ እንመልከት

> "…ካላንቺ ሚስት አላገባም ብዬ ስግደረደር
> ቆየሁ…"/ከርታታው፥312/
> "…በጣም ጥንቁቅ፣ብልህ ተማሪና ለሰው
> ተጨናቂ ነበር፡፡"/ከርታታው፥208/
> "…ለተበደሉ ተቆርቋሪ፣ለበዳዬች ደግሞ

የእግር ውስጥ እሳት ነበር።”/ከርታታው ፥225/…እነዚህ ሁሉ ሙገሳዎች በእርግጥ የእርሱን ባህሪ ሊገልፁ ይችላሉ ወይ? ተብሎ ቢጠየቅ መልሱ አይ ነው።

ከዛች የገጠር ከተማ ወጥቶ ትልቅ ከተማ አዲስ አበባ ውስጥ የግል ቤት እስከመያዝ የደረሰው ከርታታው ለምን የልጅነት ፍቅሩንና የከንፈር ወደጁ የሆነችውን ፀሀይን ይቅርታ ጠይቆ ባለቤቱ አያረጋትም ነበር? ቀልድ አዋቂነቱና ፎልፏላነቱ ብዙ ጠላቶቹን ቂም ያስረሳ እንደነበር በመጽሐፉ ተገልጿል “…ጠላቶቹ ሳይቀሩ አግባብቶ ከአፎታቸው ያወጡትን ጩቤ እንዲመልሱ ያስደርጋቸው ነበር። ብዙዎቹን እየቀለደ የሚጫወተው ስለሚያስደስታቸው ይወዳጁት እንደነበረ አስታውሳለሁ።” /ከርታታው ፥88/ ብለው የሱ ወደጅ የነበሩት ጋሼ ይማም ይገልፃሉ። ታዲያ የልጅነት የከንፈር ወዳጁን ፣ የልጁን እናት፣ ለሱ ስትል በልጅነቷ በጮርቃ እድሜዋ የመከራ ግፍ የቀመሰችውን ሴት ይቅርታ ጠይቆ ቤቱ ማስገባት ከከርታታው የህሊናዊ ባህሪ አሳሳል አንፃር ሲታይ አንባቢ የሚጠብቀውና ቢፈፀም ኖሮ ተአማኒ የሚሆን ነበር። ያ ግን ሳይሆን ቀርቶ ታሪኩ በተቃራኒው ሲነጉድ ይታያል። ደራሲው የከርታታውን ጠጪነት ወይም ለምን እንደሚጠጣ ምክንያቱ ምን እንደነበር አሳማኝነት ባለው መልኩ ሊገልፀው በመቻሉ የሚደነቅ ነው። ከርታታው የተሳለበትን ባህሪ /ሩህሩህ፣ አፍቃሪ…/ ከመሆኑ አንፃር አላማና ግቡ በትክክል የታሰበለት ቦታ ላይ አለመድረሱን ግን አንባቢው በትዝብት እንዲያይ ሆኗል። ይህም ደራሲው ቀጭን የታሪክ ገመድ ይዞ ሲበጠስበት ሌላ የታሪክ ገመድ እየፈተለና እየቀጠለ መሄዱን ያመለክታል።

### 3.2.3 የአለበል አካላዊ መልክ እና ሕሊናዊ ባህሪ

#### 3.2.3.1 የአለበል አካላዊ መልክ

በከርታታው ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ከሚገኙት ገፀ-ባህርያት መካከል ሌላው ንዑስ ገፀ-ባህሪ አለበል ነው። አለበል የከርታታውና የአያልቅበት አብሮ አደግና የቅርብ ወደጅ ነው። አለበል ከአያልቅበት ጋር በመሆን የከርታታውን የሙት መንፈስ አደራ ለመወጣት /ከዳር ለማድረስ/ ወደ ትውልድ አገራቸው ጩፋ- ስሬ የተጓዘ የሁለቱም የልብ ወዳጅ ነው። በታሪኩ የሚፈጀው መቼትም ከዋናዎቹ ገፀ-ባህሪያት ከከርታታውና ከአያልቅበት ብዙም የሰፋ አይደለም- ጠበብ ያለ ነው። ስለዚህ ስለአለበል ማለት የሚቻለው በጥቂቱ ነው።

አለበል በዚህ መጽሐፍ ውስጥ ሁለት ቦታ ብቻ አካላዊ መልኩ ተገልጾልን ይገኛል። በመጀመሪያ የሚገለፀው “…የአለበል ሆድ በመጠኑም ቢሆን ዘርጠጥ ያለ ነው። ”/ከርታታው፥112/ ይህ ገለፃ የሚያሳየን ሁለት ነገር አለ የመጀመሪያው የአለበልን ቦርጫምነት ብቻ መግለፅ ሲሆን፣ገለፃውም ለአንባቢ ምንም ምስል አይፈጥርም ምክንያቱም በቦርጫምነቱ ብቻ ምንም አይነት ትክክለኛ ምስል ማግኝት አይቻልም። በአንባቢም ዘንድ ይህ ነው የተባለ የተጨበጠ የሰው ምስል አይፈጠርምና ፤በአለባበሱስ ምን ያዘወትራል? ለተደራሲ ምንም ምስል በአይነ ሕሊና አይመጣምና። ሌላው የዚህ

ድርሰት አካላዊ መልክ ገለፃ ጉድለት በአለበል ብቻ አይመጣም በአያልቅበትም ላይ ይታያል /ይቀጥላል/፡፡

አለበል በአካላዊ መልኩ ዙሪያ መጠነኛ ገለፃ ይደረጋል፤ነገር ግን የአለበል አካላዊ ገለፃ ስግብግብነቱ ምን ያህል እንደጐዳው ለማሳየት /ለማጉላት/ ወይም የስግብግብነቱን ውስጣዊ ባህሪ የበለጠ ለማጉላት ብቻ ሲባል የመጣ መሆኑ ጥሩ ገለፃ ነው ቢያስብልም ያም ገለፃ ቦርጩን ብቻ ስለሚያመለክት ገለፃውን ልፍስፍስ ያረገዋል፡፡

በሁለተኛ ደረጃ የምናገኘው አካላዊ ገለፃው በሌላዋ ንዑስ ገፀ-ባህሪ የተሰጠው ገለፃ ነው፡፡ "...ይህን ያጐፈረውን ቂምህን የምትላጨው መቼ ነው..."/ገፅ ፥ 298/ ትለዋለች ቢያንስ እዚህ ጋር በቂሙ አስታኮ ኢ-ርቱዕ በሆነ መንገድ የፊቱን ትንሽ መሆን ወይ ትልቅ መሆን ፣የከንፈሩን ሁኔታ፣የጥርሱን ፣የአይኑን... በአጠቃላይ የፊት ገፅታ መግለፅ ይቻል ነበር፡፡

እነዚህ ሁለት ገለፃዎች በትክክል የአለበልን የአካላዊ መልክ ገለፃ ስለማያሳዩ አለበል ምን አይነት ሰው እንደሆነ በተደራሲ አይነ ህሊና ውስጥ ይህ ነው የሚባል ምንም ምስል አይከስትም፡፡ ህሊናዊ ባህሪውን /ገብጋባነቱን/ ለመግለፅ የተጠቀመበት የቦርጭ ገለፃ ግን የሚደነቅ ነው፡፡

### 3.2.3.2 የአለበል ሕሊናዊ ባህሪ

አለበል በዚህ ድርሰት ታሪክ ውስጥ ለአያልቅበት ደጋፊ፣ረዳት ሆኖ የመጣ ገፀ-ባህሪ ተደርጐ ነው የተሳለው፡፡ አያልቅበት ከከርታታው በኩል የተጣለበትን አደራ በመጀመሪያ ያማከረው ለሱ ነው፡፡ ያን አደራውን ከግብ ለማድርስ ከጐኑ ሆኖ የአያልቅበትን ጉደሎነት የሞላለት ሰው ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለአያልቅበት አላማ ግብ መምታት እንደ ዋና አጋዥ ሀይል ሆኖታል፡፡ /ይህም የአስተኔ ገፀ-ባህርያት ዋና ሥራ በአጃቢነት መቅረብ ሆኖ የዋናውን ገፀ-ባህሪ ክፍተት መሙላት ነው፡፡/ በሌላ አባባል አያልቅበት ስሜታዊ ሲሆን /ሲግል/ የሚያበርደውና መስመረ የሚያሲዘው አለበል ነው፡፡ እንዲህ ብናደርግስ እያለ ሃሳብ የሚሰጠው አይነት ሰውም ጭምር ነው፡፡ ለምሳሌ በታሪኩ ውስጥ በአቶብስ ተራ በገጠማቸው የእቃ ጫኝና አውራጆች ግብ ግብ ወቅት እንዳይጋጭና ነገር እንዳያበላሽ እንዲህ ብሎት መናገሩን በገለፃው የሚታወስ ነው፡፡ "ኧረ እባክህ አንተ ሰው አርፈህ ተቀመጥ" /ገፅ፥51/ ብሎ ነገሩን እንዲያበርድ አርጐታል፡፡

በሌላ በኩል ደራሲው በአለበል በኩል ሊያስተላልፉልን የፈለጉት መልዕክት ማንም ሰው አላማው ከግቡ እስኪደርስ እስከ ሞትም ቢሆን መስዋዕትነት መክፈል እንዳለበት አሳይተውናል፡፡ ገብጋባነትን ግን በመኮነን፡፡

አለበል የሰው ነገር የማይሰማና የስግብግብነት ባህሪ ስለሚያጠቃው፤ብዙውን ጊዜም ለሆዱ ቅድሚያ በመስጠቱ ምክንያት ለከፋ ጉዳት ሲዳረግና ሲፀፀትም ይታያል፡፡ በዚህም የተነሳ በመጽሐፉ ታሪክ ውስጥ እሱና አያልቅበት በአንድ ሆቴል ምግብ አዘው አያልቅበት

'ይቅርብህ አትብላ' ያለውን ምግብ በልቶ እስከ ሞት የደረሰበትንና ጉዞውን ያስተጓጐለበት የሚጠቀስ ነው፡፡ "…እኔ የሰው ነገር ስለማልሰማ ነው እንጂ አንተም ነግረኸኝ ነበር፡፡ …"/ገፅ፥113/ ይለዋል፡፡ ይህ አገላለፅም ይበልጥ የአለበልን ስገብጋባነት የሚያጐላው ነው፡፡

አለበል ለአላማው ቆራጥ ሆኖ የተሳለም ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ የተመረዘ ምግብ በመመገቡ እስከሞት አፋፍ ደርሶ የተመለሰው የተጠላበትን የሙት መንፈስ አደራ ከግብ ለማድረስ ነው፡፡ አለበል ለአላማው ቆራጥ፣ለአደራ የሚበቃ ገፀ-ባህሪ መሆኑን በሚከተለው የአያልቅበት ገለፃ ማረጋረጥም ይቻላል፡፡ "…አንተም እኮ ከሞት አፋፍ ደርሰህ የተመለስከው ከርታታው የጣለብንን አደራ ለመወጣት እንጂ የግል ጥቅም ኖሮህ አይደለም…"/ገፅ፥275/

### 3.2.4 የጨቡዴ አካላዊ መልክ እና ሕሊናዊ ባህሪ

በዚህ ድርሰት ታሪክ ውስጥ በአራተኛ ደረጃ የምናገኘው ሌላው ንዑስ ገፀ-ባህሪ ጨቡዴ ነው፡፡ ጨቡዴ በአውቶብስ ተራ ዕቃ በማውረድና በመጫን ሥራ ላይ የሚተዳደር ገፀ-ባህሪ ሆኖ ተስሏል፡፡ ለታሪኩ አንጊነት ወሳኝ ቦታ ላይ ብቅ ያለ ገፀ-ባህሪም ጭምር ነው፡፡ እንደሌሎቹ ገፀ-ባህርያት ሰፋ ያለ ጊዜና ቦታ ባይኖረውም በተሰጠው ጥቂት መቼት አንድ ትልቅ ቁም ነገር /ልብ ሰቀላ/ ለድርሰቱ ጥሎ አልፏል ፡፡ አንባቢው የጨቡዴን የሕይወት ታሪክ በሚያነብበት ጊዜ በሕሊናው አንድ ጉዳይ ይመጣለታል፣ ጨቡዴ ማን ይሆን? የሚል ጥያቄ በመጠየቅ ማንነቱን ከከርታታው ታሪክ ጋር በማናፀር ማንነቱን ለማወቅ ይጓጓል፡፡ በዚህ ታሪክ መሠረትም አንባቢ ወደፊት ያለውን ጉዳይ እያሰበ በታሪኩ ይሳባል፣መጽሐፉን አንብቦ ለመጨረስም ይጓጓል፡፡ የጨቡዴን ማንነት ለማወቅ እና ውጤቱን ለመረዳት በልቦለዱ ታሪክ አካሄድ ልብ ሊባል የሚገባው ጉዳይ ነው "ስሜቱን በሳቡት ሰዎች ላይ የሚደርስባቸውን ሁኔታ የማወቅ ጉጉት በአንባቢው ተፈጥሮ ውስጥ ያለ ፍላጐት ነው" /ዘረሁን፥157/ ብሏል፡፡

### 3.2.4.1 የጨቡዴ አካላዊ መልክ

ይህ የጨቡዴ አካላዊ መልክ ገለፃ ወደፊት ለምናነሳው በመጽሐፉ ውስጥ ስላሉ ገፀ-ባህርያት የአካልና የሕሊና ተመሳስሎ ትልቅ መረጃ ይሆነናል፡፡ ጨቡዴ በውቶብስ ተራ የተሰማራ ዕቃ አውራጅና ጫኝ ሠራተኛ ነው፡፡ ዋናው የአካላዊ መልኩ የተነሳበት ጉዳይ አካላዊ መልኩና ሕሊናዊ ስብዕናው አብሮ የማይሄድ በመሆኑ ነው፡፡ አንባቢ አካላዊ ገለፃውን እና ከሚፈጥራቸው ድርጊቶች (ከስብዕናው) እጅግ የተቃረነ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ የጨቡዴን አካል ክፍል የተናደደ ጊዜ ማየት በቂ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በአጠቃላይ ሰውነቱ አስፈሪና አርበትባች መሆኑ እንደሚከተለው ተገልፆ ይገኛል፡፡

> "… ፊቱ ጠይምነቱን ወደ ጥቁረነት አስተላለፈ በፊቱና በአንገቱ ላይ ያሉ ጅማቶችም ተገታተሩ … ሰውነቱ ወባ እንደያዘው ሰው ሲንዘፈዘፍ ያግዙፍ ሰውነቱ እየተቆረጠ የሚወድቅ መሰለ…" /ከርታታው *62/

#### 3.2.4.2 የጨቡዴ ሕሊናዊ ባህሪ

የጨቡዴን ስብዕና ከከረታታው ስብዕና ጋር አንባቢ እያነፃፀረ ጨቡዴ ማነው? የሚለውን ጥያቄ በመጠየቅ መልስ የሚያገኝበትና የጨቡዴን ማንነት ከሌሎች ገፀ-ባህርያት ጋር በማዛመድ የደራሲው የገፀ-ባህርያት ህሊናዊ ባህሪን አሳሳል ተመሳስሎ የሚቃኝበት ነው፡፡ ጨቡዴ ብዙ የሕይወት ፍልስፍናዎች፣ የረቀቀ አስተሳሰብ ፣ ፖለቲካዊ አቋሙ የበሰለ፣ ማህበራዊ አመለካከቱ የጠለቀ ለሰዎች አዘኝና ተቆርቋሪ ሆኖ የተሳለ ገፀ-ባህሪ ነው፡፡ በዛ ቦታ ላይ ሊያስቀምጡት የማይቻል እልኸኛና ግልፍተኛ ሆኖም ተቀርጿል፡ ፡ ጨቡዴ ብዙ ከማንበብና በትምህርት ያዳበረውን ዕውቀቱን ያለቦታው የሚገልፅ ሆኖም ተስሏል፡፡ ከቅን አስተሳሰብና አመለካከቱ ውጪ የሆነው ግልፍተኛነቱና እልኸኝነቱ ከተቀረፀበት ባህሪ አንፃር ወጥ አለመሆኑ አንባቢን ጥያቄ እንዲያነሳ ያረጋል፡፡ በትርፍ ጊዜውም የዩንቨርሲቲ ተማሪ እንደሆነ በታሪኩ ተገልፆ ይገኛል፡፡

> "… በትርፍ ጊዜዬ ያለመሰልቸት ልዩ ልዩ መጽሐፍትንና ጋዜጦችን ስለማነብ በአለም ላይ ያለማቋረጥ የሚላወሱትን መጥፎም ሆኑ ጥሩ ድርጊቶችን እከታተላለሁ፡፡…በከፍተኛ ማዕረግ ከዩንቨርሲቲ እንደምመረቅ እርግጠኛ ነኝ፡፡" /ከርታታው *64/

ተብሎ የተገለፀለት ይህቀረህ የማይባል ስብዕና ባለቤት የሆነው ጨቡዴ በመማሩና በማንበቡ ይህ ነው የማይባል ከሱ የማይጠበቅ ስራ ሲሰራ (ግልፍተኛና እልኸኛ) የሚታይ ንዑስ ገፀ-ባህሪ ሆኖ ተስሏል፡፡

#### 3.2.4.3 ጨቡዴ ለድርሰቱ ያመጣው ፋይዳ

እነአያልቅበት የከርታታውን የዘር ሀረግ ለመፈለግ ወደ ደሴ በሚጓዙበት ወቀት አውቆብስ ተራ የከረታታውን አይነት ባህሪና አስተሳሳብ የተላበሰ ሌላ ወጣት ያገኛሉ፡፡ ይህ ወጣት ከርታታው ከሚኖርበት አካባቢ ወልዲያ የመጣ ሲሆን በአጠቃላይ የመፅሀፉ ታሪክ ላይም አንዳች አጓጊነትን ፈጥሯል፡፡ አንባቢ አንድ ጥያቄ እንዲጠይቅም አርጓል፡፡ ከከርታታው ታሪክ በመነሳት ጨቡዴ የከርታታው ልጅ ይሆን? የሚል፡፡

አንባቢ የዚህን ወጣት የትውልድ ቦታና ታሪክ በመጽሐፉ ሲሰማ አንዳች ነገር በልቡ ይጠራጠራል፣ ተጠራጥሮም አያበቃ በታሪኩ ይሳባል፣ ይጓጓል፡፡ በአእምሮው ውሰጥም የሆነ ጥያቄን ያጭራል፡፡ ጨቡዴ የጠቀሳላው የመፅሐፉ ታሪክ አካል ይሆን? የሚል፡፡ በዚህ የተነሳም ታሪኩን ለማንበብ /ለመቀጠል/ ይነሳሳል፡፡ ይህንን ጉዳይ አያልቅበት ሲያጠናክረው እንዲህ ይለናል፡፡ "… የከርታታውን ታሪክ ለመቃረም በምንዳክርበት ጊዜ የሌላ ከርታታ ታሪክ አገኘን፡፡ ወይ አጋጣሚ!" /ከርታታው *66/ ብሎ በአንጥልጥል በመተው ተደራሲውንም ያጓጓል፡፡

### 3.2.5 አብዬ ሃምዛ

በዚህ ልቦለድ ደርሰት የሽማግሌ ገፀ-ባህሪያትን ወክለው ከተሳሉት አዛውንት ገፀ-ባህሪ መካከል አንዱና ዋነኛው ናቸው፡፡ ዕድሜያቸው ወደ ዘጠና አካባቢ ይጠጋል የተባሉት እኚህ ገፀ-ባህሪ በአካላዊ መልካቸው አገላለፅ የድርሰቱ ቅርፅና መጠን ከሚፈቅደው እጅግ በላቀ መልኩ የተሳሉ ሆነው ይገኛሉ፡፡ ከዚህ ድርሰት ታሪክ ጋር በጣም ተያያዥነት ያላቸው ንዑስ አዛውንት ገፀ-ባህሪ ናቸው፡፡ ለነአያልቅበት የመረጃ ምንጭ፣ ማሪፊያ ቦታና አማካሪ የሆኑ በሕይወታቸው ብዙ ያዩ የታሪክ አባት ናቸው፡፡ ለአያልቅበት የሙት መንፈስ አደራ ግብ መምታት የአብዬ ሀምዛ በታሪኩ መኖር ተገቢና አስፈላጊ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ ምክንያቱም ለከርታታው የከንፈር ወዳጅና ለልጁ እንዲሁም ለእናቱ በሕይወት መገኘት ቁልፉን ሚና የምትጫወተው የዘነበች አያት ስለሆኑ፡፡

3.2.5.1 **የአብዬ ሃምዛ አካላዊ መልክ**

የገፀ-ባህሪው አካላዊ መልክ ገለፃ የዘመናዊ ልቦለድ የገፀ-ባህሪ አገላለጽን ሕግ የማይጠብቅ አካላዊ መልካቸው በሙሉ በአንድ አንቀፅ ተዘርዝሮ ይገኛል፡፡ ይህ የመልክ ገለፃቸው በጣም የተዘረዘረና የበዛ መሆኑ አንባቢን ያሰለቻል፡፡  ከራስ ፀጉር እስከ እግር ጥፍር በመገለፃቸው ተንዛዝቷል፡፡ የአካላዊ መልካቸው እየተከፋፈለ በሌላ ገፅ ቢገለጽ ኖሮ ለአንባቢ የተመቸ ይሆን ነበር፡፡ ይህ አካላዊ ገለፃ ወደፊት ከምናየው የገፀ-ባህርያት የአካል ገለፃ ተመሳስሎ ጋር ትልቅ መረጃ የሚሆን ሆኖ የሰውነት /የቁመታቸው/ ኽርጋዳነትም ለዚህ የደራሲው የገፀ-ባህርያትን የአካል ማንነት ገለፃ ከአንድ ባህር የቀዳ እስኪያስመስለው የአካል ገለፃው ተመሳሳይነት ለልብወለዱ የተአማኒነት ጉዳይ ያስነሳ ሆኗል፡፡ ተራኪው አያልቅበትም የገፀ-ባህሪውን የአካል ገለፃ በሚከተለው መልኩ አሳይቶናል- ስዕላዊነት በተላበሰ መልኩ፡-

> “… ቁመታቸው ጆርጋዳ ቀጭንና መልከ ሰልካካ ናቸው፡፡ የራስቸው በራ በመጠኑም ቢሆን ገባ ያለ ቢሆንም የቀረው ፀጉራቸው ተንጨፍሮ የባዘቶ ጥጥ ይመስላል፡፡ ግንባራቸው ሰፋ ያለ ሲሆን አፍንጫቸው ስንደዶ የመሰለ ነው…፡፡አልፎ አልፎ እጆቻቸው ሲንቀጠቀጡ ይታያሉ፡፡ …አጠር ያለው አንገታቸው በመጠኑም ቢሆን ሽብሽቧል፡፡” /ከርታታው*136/

ብሎተራኪው የተመለከተውን አከላዊ ማንነት ዝርግፍ አርጐ ያመጣል፡፡

3.2.5.2 <u>**የአብዬ ሃምዛ ሕሊናዊ ባህሪ**</u>

በመጽሐፉ ታሪክ የኚህ አዛውንት መምጣት ለድርሰቱ የታሪክ ፍሰት መቋጫ ማግኘት ደራሲው የተጠቀመበት የገፀ-ባህሪን አሳሳል ጥበብ /ዘዴ/ የተካነ መሆኑን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩልም የኚህ አዛውንት የተሳሉበት አላማ የአገርን ታሪክ ከትውልድ ትውል እንዲቀጥል፣ የሀይማኖት እኩልነትን ይህ ትውልድ እንዲረዳና እንዲገነዘብ የኑሮን፣ ባህልና የአካባቢ መራቆት ምን ያህል በማህበረሰቡ ሕይወት ላይ ያመጣውን

ተፅዕኖ ከነማስረጃው ለማሳየት ብቻ ሳይሆን የከረታታውን ዘር ከመገኘት አንፃር ሊጠቀሱ የሚገባቸው ገፀ-ባህሪም ጭምር መሆናቸው ነው፡፡

አብዬ ሃምዛ በውስጣቸው ወጣትነት የሚሰማቸው ጠንካራ አዛውንት ናቸው፡፡ በባህሪያቸው አንግዳ ተቀባይ፣ ደግ፣በዕምነታቸው ፅኑ፣ ለሞት ያላቸው አመለካከት ከፍርሃት የፀዳ፣ ያላቸውን ከሰው ተከፍለው የሚኖሩ፣ ማህበራዊ ኑሮአቸው የሚያስቀና እና ደስተኛ አዛውንት ናቸው፡፡ ይህ የአብዬ ሃምዛ ውስጣዊ ስብዕና በፊት ከታዩት ሌሎች ገፀ-ባህርያት ጋር በእጅጉ የተመሳሰለ መሆን የደራሲውን የማሕበራዊ ኑሮ አመለካከቱን የተገደበ ያረገዋል፡፡ ገፀ-ባህሪው ይሄን ሁሉ የቀናና የተስተካከለ ባህሪ ያገኙት ብዙ ነገስታትን እና መንግስታትን ያሳለፉ በመሆናቸው ብቻ ሳይሆን የጠቅላላ ዕውቀታቸውን የሚያስፋ ነገር ከመገናኛ ብዙሃን ስለሚከታተሉም ጭምር ነው፡፡ ይህም ከመፅሀፉ እንዲህ ተገልፆ ይገኛል፡፡ "... በውስጦቸው ወጣትነት የሚሰማቸው ፤የሚናገሩትን አጣርተው የሚያውቁና በየቀኑ በራዲዩ የሚተላለፈው የአለም ዜና የማያመልጣቸው ብልህ አዛውንት ናቸው፡፡" /ገፅ*136/

### 3.2.6 የዘነበች አካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ

ለዚህ ድርሰት ታሪክ መቋጫ ማግኘት ሌላዋ ተጠቃሽ ገፀ-ባህሪ ዘነበች ነች፡፡ የተማረችና የአብዬ ሃምዛ የልጅ ልጅ ነች፡፡ ከብዙ የመጽሐፉ ንዑስ ገፀ-ባህርያት መካከል ግንባር ቀደሟ እሷ ነች፡፡ የከርታታውን የዘር ሀረግ ለመፈለግ ለመጡት ለነአያልቅበት ከፍተኛ እገዛና ዕርዳታ አርጋለች፡፡ ለታሪኩ ፍፃሜ መስመር መያዝ ትልቁንና አብዬን ሚና ተጫውታለች፡፡ ይህም ገፀ-ባህሪዋ የመጣችበትን ጉዳይ ከውና በአግባቡ ጨርሳለች፡፡

#### 3.2.6.1 የዘነበች አካላዊ መልክ

በዚህ ድርሰት እጅግ ብዙ ቦታ አካላዊ መልኳ በመገለፅ ቀዳሚዋ ገፀ-ባህሪም ነች፡፡ በተለያዩ ገፆችና በተለያዩ ሰዎችም /ገፀ-ባህርያት/ በመገለፁም ቀዳሚዋ እሷ ነች፡፡ በአያልቅበት፣ በወ/ሮ ሸዋዬና በአለበል በተለያዩ ቦታዎች ተገልፃለች፡፡ ይህች ገፀ-ባህሪ በአንድ አንቀጽ ብቻም በመገለጿ የገፀ-ባህሪያት አቅራረፅ ስልት ላይ ትልቅ ጥያቄ አምጥታለች፡፡ ምክንያቱም የአካላዊ ማንነቷ ገለፃ ዘመናዊውን አገላለጽ ዘዴ ባለመላበሱ ያስተቻል፡፡ የዘነበችን አካላዊ ማንነት ከገለፁት መካከል ለዋቢነት አያልቅበት የገለፀውን እንመልከት፡-

> "... ዘነበች እግዜር ያልተስተካከለው ሰውነትሽ የትላይ ነው እያለ የፈጠራት ትመስላለች፡ ዘነበች ቁመቷ ዘለል ያለ ሆኖ የሰውነቷ ቅርፅ የደስ ደስ ያለውና ውብ ነው፡፡ ... ዘነበች እዚህ ላይ ጉድሎሻል የማትባል ቁንጅናና ደምግባትን በማዋሀድ ንቅስ ተደርጋ የተፈጠረች ናት፡፡" /ከርታታው * 180/

#### 3.2.6.2 የዘነበች ሕሊናዊ ባህሪ

ዘነበች ያላገባችና ዕድሜዋ ወደ ሰላሳ ሁለት የሚጠጋ ሴት ነች። ያለዕድሜ ጋብቻን በመቃወም ከትውልድ ሀገሯ በመጥፋት ትምህርቷን የተማረች፣ ስለሴት ልጆች ስለህይማኖትና ስለተፈጥሮ ያላት አመለካከት ለብዙዎች የአካባቢው ሴትም ትልቅ ተምሳሌት እንድትሆን ተደርጋ ተስላለች። የዘነበች ሕሊናዊ ባህሪ በወ/ሮ ሸዋዬ እንዲህ ተገልጾ እናገኛለን "... አንቺ ግን እምቢ አሻፈረኝ ብለሽ ተሰርቀሽ በመጥፋት ወደ ደሴ ኮብልለሽ ትምህርት ቤት ገባሽ፡፡ "/ገጽ 220/

### 3.2.7 በከርታታው ልብወለድ ውስጥ የገፀ-ባህርያት

### አሳሳል መመሳሰል በአካላዊ መልክና ሕሊናዊ ባህሪ

በመሠረታዊነት አንድ የልቦለድ ድርሰት መጽሐፍ ደራሲ የሆነ ሰው ልቦለድ ድርሰቱ ዘመን ተሻጋሪ /Classic Novel/ እንዲሆንለት ከፈለገ ከጅማሬው እስከ ፍፃሜው ድረስ እጅግ ጥንቃቄ በተሞላበት /በጣም በተጠና/ መልኩ ድርሰቱ የሚያስፈልጋቸውን አለባውያን ማወቅ አለበት። ታሪክ፣ ገፀ-ባህሪ፣ግጭት... የተሟሉና የተጠኑ አርጎ ማዘጋጀት፤ እንዲሁም ራሱ መዘጋጀት አለበት። ታሪክ ፈጠራ ላይ በተለየ መልኩ ጥንቃቄ ማድረግ አለበት ገፀ-ባህርያት ያለታሪክ አይኖሩምና።

ታሪክ የሌለው ድርሰት የልጆች እቃቃ ጨዋታ አይነት ምስቅልቅሉ እንደሚጠፋ ሁሉ ግጭት የሌለው ታሪክም እንዲሁ ነው።

ታዲያ ታሪኩንም በታሪኩ ውስጥ ያሉትን የተለያዩ የግጭት ደረጃዎችን የሚከውኑልንና ለአንባቢ የተፈለገውን መልዕክት የሚያስተላልፉልን በልቦለዱ ውስጥ የተሳሉት ገፀ-ባህርያት እንደመሆናቸው መጠን አንድ ደራሲ የድርሰት ስራውን በሚከውንበት ወቅት ሁሉ ስለሚስላቸው ገፀ-ባህርያት ማንነትና ምንነት ጠንቅቆ ማወቅ አለበት። እንዲሁ ከአንድ ባህር የተቀዱ አይነት በማስመሰል መሳል ያስጠይቃል።

> "ደራሲ ገፀ-ባህርያት በሚቀርፅበት ጊዜ ምርጫ ያደርጋል። ከተመለከታቸው ሰዎች መሀል ለፈለገው አላማ ግብ መች ይሆናሉ ብሎ ያመነባቸውን ወይም ገፀ-ባህሪውን በውል ሊያሳዩ ይችላሉ የሚላቸውን የተወሰኑ አካላዊና ህሊናዊ መልኮችን ብቻ መርጦ ይወስናል። የሰውን ባህሪያት በሙሉ ማሳየትም አዳጋች በመሆኑ ምርጫው አንዱን ገፀ-ባህሪ ከሌላው ለይተው በሚያሳዩ አበይት ባህርያት ላይ ብቻ ማተኮር ይኖርበታል፡፡/ዘሪሁን *161

ይህ መሆን እንዳለበት እየታወቀ በዚህ <u>በከርታታው</u> ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ላይ የምናገኛቸው አብዛኛዎቹ ገፀ-ባህርያት የአካላዊ መልካም ሆነ የህሊናዊ ባህሪያቸው በአመዛኙ መልኩ ተመሳሳይነት ታይቶባቸዋል። ይህም የደራሲውን በማህበረሰቡ ውስጥ ንቁ ተመልካችነት የት ድረስ ነው ያስብላል።

#### 3.2.7.1 የከርታታው፣ የአያልቅበትና የአያልቅበት

**አባት ህሊናዊ ባህሪ መመሳሰል**

> "… ደግነትህ፣ርህራሄህና፣ሰላምን ለመፍጠር ታደርገው
> የነበረው… ድፍረትህ …" /ከርታታው *25/
> "በጣም ጥንቁቅ፣ ብልህ ተማሪና ለሰው ተጨ
> ናቂ ነበር።" /ከርታታው *208/

ይህ የከርታታው የባህሪ ገለፃ በአመዛኙ ከአያልቅበት አባት ጋር ይመሳሰላል።

> "… አባትህ አለሙ ሩህሩህና ቸር ሰው ነበር … ለተቸገረ እጁን የማያጥፍ … ታማኝነትን፣ ሀቅን ርህራሄንና ደግነትን አስተምሮ አልፏል።" /ከርታታው *127/

የአያልቅበት ህሊናዊ ባህሪ ከከርታታውና ከእባቱ ከአቶ አለሙ ጋር የተመሳሰለበት ባህሪ በወ/ሮ ጀማነሽ እንዲህ ተገልጾል…" አያልቅበት እንደ ስሙ ትህትናው፣ ደግነቱ፣ ቁምነገሩ ፍቅሩ የማይነጠፍ ሰው ነው።" /ከርታታው*248/

እንዲህ እያደረገ የገፀ-ባህርያቱን ህሊናዊ ባህሪ የገለፀልን ደራሲ ራሱ አያልቅበት የተባለውንም ገፀ-ባህሪ ትሁት፣ ደግ፣ቁምነገረኛ ቃሉን ጠባቂና ፍቅሩ የማይነጥፍ አድርጐ ህሊናዊ ባህሪውን ከሳለው በኂላ፣ በየምዕራፉና በየገፁ የምናገኛቸውን አዳዲስ ገፀ-ባህርያትም ህሊናዊ ባህሪ ከተመሳሳይ ባህር ቀድቶ አምጥቶልናል፤ያም በመሆኑ ገፀ-ባህርያቱ ተመሳሳይ የሆነ የባህሪ ውርስ ዝምድና ስላላቸው ወደ ልቦለዱ መሠረታዊ ነገር /ታሪኩን ወደ ፊት እንዲሄድ ከሚያደርገው አንኒ ጉዳይ/ወደ ግጭት እንዳይገቡ አድርጓቸዋል።። ይህም ደራሲው በሥራው ላይ ያሳየው ስነጽሑፋዊ ድክመት ነው። በተለይ በገፀ-ባህሪ አሳሳል ላይ።

**3.2.7.2 የጨቡዴ፣ የአብዬ ሀምዛና የዘነበች**

**አካላዊ መልክና ህሊናዊ ባህሪ አሳሳል መመሳሰል**

በአንድ ልቦለድ ታሪክ ውስጥ ደራሲው የሚፈልገውን መልዕክት በትክክል ያስተላልፉልኛል ብሎ የሚመርጣቸውን ገፀ-ባህርያት በአንባቢ አእምሮ ውስጥ ተስለው እና ተቀርፀው እንዲቆዩ ለማድርግ የራሳቸው የሆነ ስብዕና፣ የራሳቸው የሆነ መልክ፣ የራሳቸው የሆነ መነሻና መድርሻ የታሪክ ሰንሰለት ሊኖራቸው ግድ ይላል።

> "… በገፀ -ባህሪ አቀራረፅ ሌላው መታወቅ ያለበት ጉዳይ ገፀ-ባህሪያት በሰብዕና መልካቸው ፍፁም ወይም አንድ ወጥ ሆነው መሳል የሌለባቸው መሆኑን ነው። የእውን ዓለም ሰዎች በሰብዕናቸው አንድ ወጥ አይደሉም ፤ የሰናይናየእኩይ ፣ የጠንካራና የደካማ ባህሪያት ጥንቅር ናቸው። በድርጊታቸውም ሆነ በባህሪያቸው በጐና ክፉ ተጣምረው ይገኙባቸዋል።…" /ዘሪሁን*163/

ይህ ሆኖ እያለ ግን በከርታታው ልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ የተሳሉት ገፀ-ባህርያት በሰብዕና መልኮቻቸው ፍፁም አንድ ወጥ ከመሆናቸው በዘለለ መልኩ፣ አንዱ ገፀ-ባህሪ ከሌላው ገፀ-ባህሪ ጋር ያለው አካላዊ መልክም ሆነ ህሊናዊ ባህሪ ላይ የተቀራረበና መመሳሰል ይታይባቸዋል፡፡ይህም አንዱን ከአንዱ ለመለየት እስከሚያስቸግር ድርስ ያደርሳል፡፡ "… ፊቱ ጠይምነቱን ወደ ጥቁርነት አስተላለፈ፡፡በፊቱናበአንገቱ ላይ ያሉት ጅማቶች ተገታተሩ፡፡…… ያ ግዙፍ ሰውነቱ እየተቆረጠ የሚወድቅ መሰለ …" /ከርታታው*62/

ይህ የጨቡዴ አካላዊ መልክ ገለፃ ከታች ከምንመለከተው የአብዬ ሀምዘና የዘነበች አካላዊ መልክ ገለፃ ጋር በጣም የተመሳሰለ ሆኖ እናገኘዋለን፡-

"… ቁመተ ጀርጋዳ ቀጭንና መልከ ሰልካካ ናቸው፡፡…"

/ከርታታው *135/

"ዘነበች ቁመቷ ዘለል ያለ ሆኖ የሰውነቷ ቅርፅ …" /ከርታታው *179/

'ግዙፍ ሰውነቱ' የሚለው የጨቡዴ አካላዊ ገለፃ 'ቁመተ ጀርጋዳ' የሚለው የአብዬ ሀምዛ የቁመት ገለፃ 'ቁመቷ ዘለል' የሚለው የዘነበች አካላዊ ገለፃና … "ቁመቱ ዛላው፣ የራሱ ሾጣጣነት የግንባሩ ስፋት…" /ከርታታው *32/ የከርታታው አካላዊ ገለፃ የቁመታቸውን መርዘም የሚያመለክት ነው፡፡ በሌላ በኩል የሁለቱ ዋነኛ ገፀ-ባህሪያት የከርታታውና የአያልቅበት የፊት ከለር መመሳሰል በደራሲው የገፀ-ባህሪይ አሳሳል ላይ ትልቅ ጥያቄ ያመጣል፡፡ የደራሲውን በማህበረሰቡ ያሉ (የገሀዱ አለም ሰዎችን) ሰፋ አርጐ የመመልከትን አቅም ከግምት ውስጥ ያስገባል፡፡

"… ከሳና በጨጭ ከማለቱ በስተቀር ቁርጥ ያው ራሱ
ከርታታው ነው!" /ከርታታው *32/"…

"…የሚጠሩኝም ቢጫ እያሉ ነበር" /ከርታታው *246/

እነኚህ ከላይ የተጠቀሱት የከርታታውና የአያልቅበት የፊት ከለር ገለፃዎች ናቸው፡፡ 'በጨጭ' እና 'ቢጫ' የሚሉት ቃላት ሁለቱም ቀይ ናቸው ወደሚል ድምዳሜ ያደርሳልና፡፡

የልቦለዱ ገፀ-ባህሪያት አካላዊ መልክ አሳሳል በዛ በሚል ሁኔታ ቁመታቸው ረጃጅሞች፣ የፊት ከለራቸው ቀያዬች ተደርገው ሲሳሉ ህሊናዊ ባህሪያቸውም ቢሆን አንድ ወጥና የሁሉም ተመሳሳይነት ያለው አሳሳል ነው ለማለት ይቻላል- ልክ ከአንድ ባህር የተቀዱ አይነት ያስመስላቸዋል፡፡

**ጨቡዴ**

"… በትርፍ ጊዜዬ ያለመሰልቸት ልዩልዩ መጽሐፎችንና ጋዜጦችን ስለማነብ በአለም ላይ ያለማቋረጥ የሚላወሱትን መጥፎም ሆኑ ጥሩ ድርጊቶችን እከታተላለሁ፡፡" /ከርታታው*64/

**አበዬ ሀምዛ**

"... አብዬ ሀምዛ ግን በውስጣቸው ወጣትነት የሚሰማቸው የሚናገሩትን አጣርተው የሚያውቁና በየቀኑ በራዱዩ የሚተላለፈው የዓለም ዜና የማያመልጣቸው ብስል አዛውንት ናቸው።" /ከርታታው *136/

**ዘነበች**

"... ተሰርቀሽ በመጥፋት ወደ ደሴ ኮብልለሽ
ትምህርት ቤት ገባሽ።" /ከርታታው *220/

በአጠቃላይ ሊባል በሚቻል መልኩ በመፅሀፉ ውስጥ የተሳሉት ገፀ-ባህርያት ወይ በአከላዊ መልክ አሳሳል አሊያም ደግሞ በህሊናዊ ባህሪ አሳሳል ፍፁም የሆነ ተቀራራቢነት ያለው መመሳሰል ስላላቸው በመፀሀፉ ውስጥ ግጭት እንዳይከሰት ሆኗል። በመሆኑም መጽሐፉ ከገፀ-ባህርያት የግጭት አሳሳል አንጻር ድክመት አምጥቷል።

### 3.2.8 የከርታታው ልቦለድ መፅሀፍ የገፀ-ባህርያት ስም፣ አሰያየምና የግጭት ሁኔታ

ደራሲና የስነጽሑፍ ባለሙያ የሆነው አማረ ማሞ "<u>የቀለም ጠብታ</u>" በሚል ባሳተመው መጽሐፉ ውስጥ /1976/ ማራኪ ርዕስ በሚል ሥር በቁጥር ወደ አስራ አምስት የሚሆኑ የማራኪ ርዕስ አመራረጥ መንገዶችን በጥናት ላይ ተመርኩዞ አቅርቦልን እናገኛለን። ከነዚህም አሰገራሚና አስደንጋጭ ርዕስ በሚል ትንታኔ ሰጥቷል። በተራ ቁጥር 11 ላይ አስገራሚና አስደግጋጭ ርዕስ ሲል የአስገራሚና አስደንጋጭ ርዕስ ይዘትን ገልጿል። "አስደንጋጭና አስገራሚ የሆኑ ርዕሶች የአንባቢን ስሜት ይስባሉ። "/አማረ *155/ በዚህ ገለፃ ይዘት መሠረትም የምንመድበው ይህን ከርታታውን ነው። የስሙ ትርጓሜም እንደሚያመለክተው በሕይወቱ ምንም ያልተሳካለት ገፀ-ባህሪ እንደሆነ ያሳያል። ከርታታው እድሜውን ሁሉ ሲንከራተት የኖረ አላማውን ከግቡ ሳያደርስ፣ ትዳር ሳይዝ በመጠጥ ሱስ ተለክፎ በአጭሩ፣ በአርባ ሶስት አመቱ የተቀጨ አስተዋይ፣ አሳቢ፣ ሩህሩህና ለአገር ብዙ ሊሰራ የሚችል፣ ተጫዋችና አስቂኝ ተግባቢ ከርታታ መምህር ነው፡ ፡

<u>የከርታታው</u> ልቦለድ መጽሐፍ ደራሲ በመጽሐፉ ማስተወሻ እንደገለፀው መጽሐፉ እንደቀልድ ተጀምሮ ሳይታሰብበት ያለቀ እንደሆነ አንባቢ የሚረዳው ሀቅ ነው። ገፀ-ባህሪያቱ በሃሳብም፣ በመልክም፣ በባህሪም መመሳሰል ከርታታው፣ አያልቅበት፣ ዘነበች፣ አብዬ ሀምዛ ፣ጨቡዴ፣ አቶ ይመር... እንዲሁም ሁሉም የተስተካከለ ቀና የሆነ አመለካከት መያዛቸው ደራሲው በሕይወት ዘመኑ ክፉት አጋጥሞት አያውቅም ወይ?!

ያስብላል፡፡ ገፀ-ባህርያቱን በዚህ ዓለም የሌሉ ግሩሞች አርጐ መሳሉ ለግጭት እንዳይዳረጉ አርጓል፡፡

ልቦለድ ድርሰት የገሀዱ ዓለም ነፀብራቅ ነው ብለን ካመንን የልቦለዱ ዓለም የሆኑ ገፀ-ባህርያት አሳሳልና የኑሮ ፍሰታቸው የዚህኛው ኮፒ ባይሆንም እንኳ በመጠኑ ተመሳሰሎ እንዲኖረው ግድ ይላል፡፡ ይህም ማለት በገሀዱ ዓለም አኩይ እንዳለ ሁሉ ሰናይም ወይም ክፉ እንዳለ ሁሉ በጐም እንደለው በልቦለዱ ውሰጥ መንፀባረቅ ነበረበት፡፡ በከርታታው ላይ ግን ይህ ፊፅሞ የለም፡፡ ሁሉ ነገር ምሉዕ በኩል ሆኖ ያለምንም ችግርና እንቅፋት ገፀ-ባህሪያቱ /ረጃጅሞቹና መፋፍራሞቹ፣ ቀዬቹና ጠይሞቹ/ ህይወታቸውን ተረትተረት በሚመስል መልኩ ሲኖሩት፤ አያልቅበት የተባለው ዋና ገፀ-ባህሪ የተረት አባትን የወከለ እስኪመስል ይተርክልናል፡፡ ይህ ነገር ከገፀ-ባህርያቱ አሳሳል መሳሳትና አጠጋቢ ካለመሆኑ ጋር ተደማምሮ የግጭቱ አይረቤነት ሲታከልበት ተደራሲው መጽሐፉን ሳይጨርሰው በጊዜ እንዲያስቀምጠው ይጋብዛል፡፡

## ማጠቃለያ

በአጠቃላይ በከርታታው ረጅም ልቦለድ መጽሐፍ ውስጥ ያሉ የገፀ-ባህርያት ብዛት ወደ ሃያ ሶስት የሚጠጉ ሲሆን፤ ገፀ-ባህርያቱም በተለያየ ዘዴና ብልሀት ተቀርፀው ይገኛሉ፡፡ ከሁሉም በላይ ያለምንም ሥራ እንደጠዋት ጤዛ ታይተው የጠፉ ወደ አራት የሚጠጉ ገፀ-ባህርያት ታይተዋል፡፡ ደራሲው እንዚህን ገፀ-ባህርያት ለምን እንዳመጣቸው ግራ ያጋባል፡፡ የተወሰኑ ገፀ-ባህርያት ላይ አካላዊ ገለፃ በትክክል አይታይም ፤ቢያንስ ኢ-ርቱዕ በሆነ መንገድ ባይገለፁ እንኳን ርቱዕ በሆነ መንገድ መቅረብ ነበረባቸው፡፡ ያ ግን ሳይሆን ቀርቷል አብዛኛው የውጫዊ መልክ እና የውስጣዊ ባህሪ ገለፃ በንግግር ቴክኒክ ባለመቅረቡ የአፃፃፍ ቴክኒኩን ደካማ አርጐታል፡፡ ወይ ተራኪው ራሱ ይነግረናል አልያም ሌላ ገፀ-ባህሪ ይተርክልናል፡፡ ይህም ዘዴ ለድርሰቱ ትልቅ የሆነ ድክመት አስከትሏል፡፡

በተለይ የአብይ ገፀ-ባህሪቶቹ የከረታታውና የአያልቅበት አካላዊ መልክ ገለፃ እምብዛም ጉልቶ አይታይም፡፡ ምንም እንኳን የአያልቅበት አካላዊ መልክ ገለፃ በመላጣነቱና በቀይነቱ ብቻ መውሰኑ ገለፃውን ጉደሎ ቢያደርገውም የገፀ-ባህሪውን አካላዊ ማንነት ለመግለፅ ደራሲው የተጠቀሙበት የራሳቸውን ፎቶ በሚመለከት የተጠቀሙት የገለፃ ቴክኒክ የሚደነቅ ሆኖ ተገኝቷል፡፡ በሌላ በኩል ግን የዘነበች የአካልና የስብዕና ገለፃ በጣም በዝቷል- ከሌሎቹ አንፃር ሲታይ፡፡ ይህም ሌሎች ገፀ-ባህሪያት የአካል ገለፃ ላይ ጥላ እንዲጥል አርጓል፡፡ እንዲሁም አንዳንድ ገፀ-ባህርያት ላይ ዘነበችና አብዬ ሃምዛ አካላዊ መልክ ገለፃ በአንድ ቦታ ላይ ብቻ በዝርዝር መገለፁ የታሪኩን አጓጊነት ሊቀንሰው ስለሚችል እንደድክመት ይታያል፡፡ በአጠቃላይ ደራሲው በውጫዊ አካል ገለፃ ላይ ጉድለት አሳይተዋል፡፡

በመጽሐፉ የተሳሉት አብዛኛዎቹ ገፀ-ባህርያት ቆራጥነታቸውና የአላማ ፅናታቸው እስከታሪኩ መጨረሻ በመዝለቁ ለድርሰቱ ከፍ ያለ ቦታ እንዲሰጠው አርጓል፡፡ የከርታታውን የፍቅር ፅናት፣ የአያልቅበትን ከከርታታው የተጣላበትን የፀሀይን፣ የልጁንና የእናቴን ፈልግ አዳራ ለመወጣት እስከመጨረሻው የአላማ ፅናታቸውን እናያለን፡፡ አለበል እንኳን ራሱ እስከሞት የሚያደርስ የሆድ ህመም ተከስቶበት ለአላማው ፅኑ ሆኖ ይገኛል ፡፡ ይሁንና ግን እነዚህ ሁሉ ገፀ-ባህርያት የባህሪ ተመሳሳሎ ስላላቸው እምንም ግጭት ውስጥ ሲገቡ አይታዩም፡፡

ገፀ-ባህሪያቱ በሙሉ ማለት ይቻላል ከምንም ግጭት የፀዱ መሆናቸው ልቦለዱን ተአማኒነት ያሳጣዋል፡፡ እንዴት የገሀዱ አለም ነፀብራቅ የሆኑ ገፀ-ባህርያት ያለምንም ግጭት እንደ ጅራት ውሃ የፈሳሉ? የጅረት ውሃ እንኳን ኩልል ብሎ በሚፈስበት አጋጣሚ ከአለት ጋር ይጋጫል፡፡ ገፀ-ባህርያቱ በሙሉ ግጭት ውሰጥ ገብተው ከገቡበት ግጭት በአሸናፊነት ለመውጣት የሚያደርጉት መፍጨርጨር የለም፤ ስለዚህ ከወዲያ ወዲህ ሲራወጡ ከሌሎች ገፀ-ባህሪያት ጋር አይጋጩም፡፡ ይህ ደግሞ ዝርግ እና የማያድጉ አድርጓቸዋል፡፡ ደራሲው መበዳደልና መወነጃጀል የሌለበት ፍፁም ማህበረሰብ እንዲፈጠር የተመኘ ያስመስለዋል፡፡ <u>በከርታታው</u> መጽሐፍ ውሰጥ ያሉ ገፀ-ባህርያት በሙሉ ሰናይ መሆናቸው የደራሲውን በማህበረሰቡ ያለውን አመለካከት /ንቁ ተመልካችነት/ ደካማ ያረጋዋል፡፡

በልቦለዱ ያሉ ገፀ-ባህርያት አብዛኛዎቹ የባህሪ ተመሳስሎና ተቀራራቢነት ይታይባቸዋል፡፡ ተቀራራቢና ተመሳሳይ ድርጊት ሲፈፀሙ ይታያሉ- ይህም ወደ ግጭት እንዳይገቡ ዳርጓቸዋል፡፡ ይህ ለአንዱ ገፀ-ባህሪ ያላበሰውን ባህሪ በሌላው ገፀ-ባህሪ ላይ ማላበሱ የደራሲውን ድክመት የጐላ አድርጐታል፡፡

በመጨረሻም በአንዳንድ ገፀ-ባህርያት ዙሪያ የሚታዩ ድርጉቶችና ገለፃዎች ታሪኩ ኢ-ተአማኒነት እንዳለውም አመልክቷል፡፡ አርቆ አሳቢውና ደራሲ መሆኑ የተገለፀው አያልቅበት በጨቡዴ አመላካከት ሲዋጥና በከተማው ኑሮ ሲደመም ማየት የሰውየውን ደራሲነት ከግምት ያስገባ አገላለጽ ነው፡፡ እንዲሁም ስለቤተሰቡ /ስለሚስቱ፣ ስለልጆቹ…/ ምንም አናውቅም፡፡ አለበል በጉዞው ላይ ምንም አይነት የንግግር ተሳትፎ አለማሳየቱ የተአማኒነት ጥያቄ ያስነሳል፡፡ አብዛኛዎቹ ገፀ-ባህርያት ለጭብጡ የማይናቅ አስተዋፅኦ ይዘው የቀረቡ ቢሆንም የጭብጡ ጉዳይ ግን ድርሰቱን የተአማኒነት ጥያቄ ውሰጥ ጥሎታል፡፡

በአጠቃላይ ልቦለዱ ከአማርኛ ልቦለድ ዕድገትና የአፃፃፍ ቴክኒክ አንፃር ሲታይ የተዋጣለትና ግሩም የሚባል አይደለም፡፡ አንድ አይነት /ተመሳሳይ/ አመለካከትና ባህሪ ያላቸው፣ተአማኒነት የጐደላቸው ገፀ-ባህርያት ታይተውበታልና፡፡

## ጥቅሶች በመገኛ ቋንቋቸው

1. . . .  A person represented in a story, novel, play etc . . . .
2. Every reader is interested in people, or should be, because people are the most important single factor in individual lives. In fiction, a reader, primarily interested in the individuals concerned, has a natural tendency to identify with the “hero” and to hate the “Villain” or to fell “for” or “with” one individual or group and “against” another.
3. A person in literary selection who is so fully described as, to be recognizable, understandable, and individually different from all others appearing in the same selection.

## ዋቢ ጽሑፎች


መሰሉ መንግስቱ :: (1986) "የገፀ-ባህርያት አሳሳል ብልሀት በሲሳይ ንጉሱ::" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ራሔል ኢታና:: (1995) "የቋንቋ አጠቃቀምና የገፀ-ባህርያት አቀራረፅ በሚክሎል የመቻል ሚዛን::" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ባህሩ ዘርጋው:: (1999) ከርታታው ፣ አዲስ አበባ፣ ማተሚያ ቤት አልተጠቀሰም::

አማረ ማሞ:: (1973) የልቦለድ ድርሰት አፃፃፍ መሠረታዊ መመሪያ :: አዲስ አበባ ፣ ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ቤት::

አፀደ ማሩ:: (1996) "የገፀ-ባህርያት አቀራረፅ በየምሽት እንግዳ ልቦለድ::" ለአርትስ ባችለር ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ፣ የኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ስነጽሑፍ ክፍል ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ::

ዘሪሁን አስፋው:: (1996) የስነጽሑፍ መሰረታውያን:: አዲስ አበባ ፣ ንግድ ማተሚያ ድርጅት::

ዳኛቸው ወርቁ:: (1985) የጽሑፍ ጥበብ መመሪያ:: አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት::

Harry show; Dictionary of Literary terms; mc Graw Hill Book Company; (U.S.A) New York St. Louis San Francisco, 1972